





# 2025–2026

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
## Montgomery County Public Schools

# የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መጽሔት




**በ 2029 ለሚመረቁ ተማሪዎች**

http://coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org/



**Montgomery County Public Schools**
UNLEASHING POTENTIAL

**አረንጓዴ ማልበስ!**

**ይህ መጽሔት እስከ 8ኛ ክፍል ይሠራል**

## ራእይ

ለእያንዳንዱ እና ለሁሉም ተማሪ የላቀ ህዝባዊ ትምህርት በመስጠት ትምህርትን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው የበለፀገ እንዲሆን ማዘጋጀት።

## ዋና ዋና እሴቶቻችን

ትምህርት መስጠት/እውቀት ማስጨበጥ፣
ግንኙነት ማዳበር፣
አክብሮት፣
ልቀት፣
ፍትኃዊነት።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

**ሚ/ስ ጁሊ ያንግ**
Ms. Julie Yang
**ፕሬዚደንት**
President

**ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን**
Ms. Grace Rivera-Oven
**ም/ፕሬዚደንት**
Vice President

**ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ**
Ms. Rita Montoya

**ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ**
Ms. Karla Silvestre

**ሚ/ስ ላወራ ስቲዋርት**
Mrs. Laura Stewart

**ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ**
Ms. Brenda Wolff

**ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን**
Ms. Natalie Zimmerman

**ሚ/ር ፕራኒል ሱቫርና**
Mr. Praneel Suvarna
**ተማሪ አባል**
Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

**ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)**
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
**የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት**
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

ጃኑዋሪ 2025

ውድ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ እና ለኮሌጅ እና ለስራ ስኬት ዝግጁ መሆኑ(ኗ)ን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶቻችን ለ 21ኛው ክፍለ ዘመን ተግዳሮቶች፣ ለኮሌጅ እና ለስራ ቦታ የሚያዘጋጁ የተለያዩ አሳታፊ ኮርሶችን እና ፕሮግራሞችን ይሰጣሉ። የ 2025-2026 የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መመሪያ የአካዳሚክ ልምድን ለማዳበር በአግባቡ ለመጠቀም እንዲረዳ የተነደፉ ኮርሶችን አጠቃላይ ገፅታ ይሰጣል። አንተ(ቺ)፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የትምህርት ቤት ካውንስለር አዳጋች እና አሳታፊ የትምህርት ተሞክሮ ለማቀድ አብራችሁ ስለምትሰሩ ይህንን መመሪያ በቅድሚያ መመልከት ጠቃሚ መሳሪያ ስለሆነ ተጠቀሙበት። ስለ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሥርዓተ ትምህርት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ድረገጽ ይመልከቱ፡-https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/

እባክዎ ያስታውሱ እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስላሉት የተወሰኑ የኮርስ አማራጮች መረጃ ይሰጣል። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ድረ-ገጾች ላይ የቀረበው መረጃ ስለ ማግኔት እና ሲግነቸር ፕሮግራሞች ዝርዝር የፕሮግራም መግለጫዎችን እና MCPS ውስጥ የሚሰጡትን የሙያ-ተኮር ኮርሶችን ጨምሮ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት አጠቃላይ ገጽታ ይሰጣል። በተጨማሪም፣ተማሪዎች ለመመረቅ የሚያስፈልጓቸውን ኮርሶች አሟልተው እንዲወስዱ እና በኮሌጅ/በስራ ሂደት ውስጥ እንዲረዷቸው በመርሃግብሩ ሂደት የሚያማክሩ ካውንስለሮች ይኖራሉ።

በአለምአቀፍ ማህበረሰብ ውስጥ አምራች ዜጋ እንድትሆኑ ማዘጋጀት በቁም ነገር የምንመለከተው ሃላፊነት ነው። ተማሪዎች የአካዳሚክ ችሎታቻችሁን እንድታሳድጉ እና ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና ወደ መረጣችሁት ኮሌጅ ወይም ሙያ ለመሄድ እንድታዘጋጁ MCPS ምርጥ፣ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው፣ እና ቆራጥነት ያላቸው መምህራንን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ካውንስለሮችን እና ድጋፍ የሚሰጡ የትምህርት ባለሙያዎችን በመቅጠራችን ኩራት ይሰማናል።

ለወደፊት የግል ግቦቻችሁን ለማሳካት በምትዘጋጁበት ወቅት ጠቃሚ የሆኑ ጠንካራ ኮርሶችን ለመውሰድ እንድትመዘገቡ በማበረታታት ስለወደፊት ስኬታችሁ ያለኝን መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ።

ከሠላምታ ጋር

Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools
ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)
የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት




ይህ መፅሔት/ቡክሌት ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፕሮግራም አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል። 6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለሚወስዷቸው ኮርሶች፣ እንዲሁም ተማሪዎች ማግኘት ስለሚችሉት ተመራጭ ኮርሶች፣ ከትምህርት ሠአት በኋላ ስለሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች/አክቲቪቲዎች እና ስለ ልዩ ፕሮግራሞች መግለጫ አካቷል።

"ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት የእያንዳንዱ ልጅ መሠረታዊ መብት ነው።"

—MCPS የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ራዕይ

ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንኳን ደህና መጡ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ትምህርት ቤቶች አብረው ይሠራሉ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
የትምህርት ቤት ድረገጽ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
የክትባት መስፈርቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ፈርጀ ብዙ ስርዓተ ትምህርት ተጠያቂነት፣ ኃላፊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
የተማሪ እቅድ ማውጫ ናሙና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2
አጠቃላይ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ካሪኩለም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ትምህርት መከታተል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የውጤት አሰጣጥ ሂደቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
የቤት ሥራ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ዲስትሪክት አቀፍ ምዘናዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የተማሪን ትምህርታዊ እድገት ሪፖርት ማድረግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የትምህርት ቤት ቤተመጻሕፍት ሚዲያ ፕሮግራም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች . . . . . . . . . 5
የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠቃላይ ምዘና ፕሮግራም . . . . . . . . . . . . . 5
እንግሊዝኛ ቋንቋ ለማዳበር/English Language Development (ELD) . . . . . . . . . . . 5
ውስን ትምህርት ያላቸው እና መደበኛ ትምህርት ያቋረጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች (Secondary SLIFE) . . . . 5
ልዩ ትምህርት ማስተማር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5
ሰክሽን 504 ፕላን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
አማራጭ ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የአለም አቀፍ ባካሎሬት/የመካከለኛ አመት ፕሮግራም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሶርትየም. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የተፋጠነ እና የበለጸጉ ኮርሶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
የተራዘሙ የትምህርት ዕድሎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ በት/ቤቶች መካከል የሚካሄዱ
የስፖርት ውድድሮች/ኢንተር-ስኮላስቲክ ስፖርቶች እና የአካዳሚክ ብቁነት . . . . . . . . . . 7
ጆርጅ ቢ. ቶማስ፣ ሲንየር. ትምህርት አካዳሚ “የቅዳሜ ትምህርት ቤት” . . . . . . . . . . . . 7
የተማሪዎች ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

የወደፊይ እቅድ ዝግጅት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልዩ/ስፔሻል ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
ሜሪላንድ የዲፕሎማ መስፈርቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
የኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
የኮርስ ክሬዲቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተደናቂነት/Merit ሰርተፍኬት . . . . . . . . . . . . 9
የሜሪላንድ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዎችን የመማር ብቃት እውቅና/Seal of Biliteracy . . . . . . . . . 9

### በዲፓርትመንት የሚሰጡ ኮርሶች


እንግሊዝኛ . . . . . 10
ሊተርሲ. . . . . 10
ምንባብ . . . . . 10
እንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር (ELD . . . . . 10
ሒሳብ . . . . . 11
ሳይንስ . . . . . 12
ማህበራዊ ሳይንስ/ሶሻል ስተዲስ . . . . . 13
ከቤት ውጪ በመስክ የሚሰጥ ትምህርት . . . . . 13
የአካል ማጎልመሻ ትምህርት . . . . . 14
የጤና አጠባበቅ ትምህርት . . . . . 14
የዓለም ቋንቋዎች . . . . . 14
ስነ ጥበብ . . . . . 15
የቤተሰብ እና ሸማች ተጠቃሚ/Consumer ሳይንስ . . . . . 17
የብዙሃን መገናኛ ሊተርሲ . . . . . 17
ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምሕንድስና/ኢንጅነሪንግ፣ እና ሒሳብ (STEM) . . . . . 17




የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በኮሌጅ እና በሥራ ቦታ ስኬታማ የመሆን እውቀት እና ክህሎት እንዲያዳብሩ የሚያዘጋጃቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እውቀት እንዲቀስሙ ይረዳቸዋል። ሁሉም ተማሪዎች መረጃን የመተንተን፣ ችግሮችን መጠቆም፣ መፍትሄ መፈለግ፣ ፅናት እና የትብብር ክህሎታቸውን ለማሻሻል እና ለትምህርታቸው ሃላፊነት መውሰድ እና የአካዳሚክ አቅማቸው ላይ ለመድረስ እድል ይኖራቸዋል። ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በጉርምስና/በኮረዳነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶችን አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ፍላጎቶችን እና ባህሪያትን ለመቃኘት ጠንካራ እና ፈታኝ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን፣ ተመራጭ ኮርሶችን፣ ልዩ/ስፔሻል ፕሮግራሞችን፣ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን እና ስፖርቶችን ያስተምራሉ።

ይህ መፅሔት/ቡክሌት ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራም አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣል። 6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚወስዷቸውን ኮርሶች፣ እንዲሁም ለተማሪዎች ያሉትን ተመራጭ ኮርሶች፣ ከትምህርት ሰአት በኋላ ስለሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች እና ልዩ ፕሮግራሞች ይገልጻል። በሁሉም ትምህርት ቤቶች ሁሉም ፕሮግራሞች እና ተመራጭ ኮርሶች አይሰጡም። ምን አይነት ኮርሶችን እንደሚሰጡ ለማወቅ ከልጅዎ ትምህርት ቤት ያረጋግጡ።

በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ስለሚሰጡ ኮርሶች እና የኮርስ መግለጫዎች ተጨማሪ መረጃ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፦ www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/index.aspx

## ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ትምህርት ቤቶች በትብብር አብረው ይሠራሉ

ልጆቻችን በሙሉ በት/ቤት እና በህይወት ስኬታማ እንዲሆኑ እንፈልጋለን። ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን እድገት እና ስኬት መደገፍ ይችላሉ።

- ትምህርት ቀዳሚ ነገር መሆኑን ከልጆችዎ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅ እና ቀዳሚ ተግባር መሆን እንዳለበት እንዲገነዘቡ ያድርጓቸው።
- ልጅዎ አዳጋች ሥራዎችን እንዲያጠናቅቅ/እንድታጠናቅቅ ያበረታቱ፣
- የልጅዎን ትምህርትዊ እድገት፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ደህንነትን ለማወቅ—ከእያንዳንዱ ልጅ ጋር ለመነጋገር በየቀኑ ጊዜ መመደብ ያስፈልጋል፣
- ለልጅዎ ጸጥ ያለ የጥናት ቦታ መስጠት እና በቤት ስራ መርዳት፣
- ልጅዎ ቴክኖሎጂን በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መደገፍ
  - የልጅዎን የኢንተርኔት አጠቃቀም፣ የማህበራዊ ሚዲያ እና አውታረ መረብ/ኔትዎርኪንግ፣ እና የሞባይል ስልክ፣ የጽሁፍ መልእክት አጠቃ ቀምን መከታተል፤
  - ልጅዎ ቴሌቪዥን የሚያይበትን/የምታይበትን ጊዜ መገደብ እና ከልጅዎ ጋር ስለ ፕሮግራሞቹ መወያየት፣
- በማህበራዊ ሚዲያ ወይም በሌሎች የመዝናኛ መድረኮች ላይ የልጅዎን የስክሪን ጊዜ መጠን መገደብ።
- ልጅዎን ከመደበኛ ትምህርት ውጭ በበጎ ፈቃደኝነት እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ፣ እንዲሁም በትምህርት ቤት በበጎ ፈቃደኝነት እንዲሰራ/እንድትሰራ ማበረታታት፣




- በቤት ውስጥ ጤናማ ልምዶችን መተግበር፣
- ልጅዎን ክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ የትምህርት ቤት አካዳሚያዊ እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ተቀባይ ከመሆን ያለፈ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን/እንድትሆን ማበረታታት።

በተጨማሪ፣ እርስዎ እና ልጅዎ በዚህ ድረገጽ ላይ የሚገኙትን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር መመሪያ፣ MCPS ውስጥ የተማሪዎች መብት እና ሀላፊነቶች መመሪያ፣ የሀይማኖት ልዩነትን ስለማክበር መመሪያ እና የተማሪ ጾታ ማንነት መመሪያ፡ www.montgomeryschoolsmd.org/students/rights/፣ ማንበብ እና በተጨማሪም የልጆችዎን ትምህርት ቤት የስነምግባር ደንብ በጋራ መገምገም አለባችሁ።

## የትምህርት ቤት ድረገጽ

ስለ ትምህርት ቤት ሲስተም እና ስለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በአጠቃላይ ጠቃሚ መረጃ በነዚህ ድረገጾች ላይ ይገኛል፦ www.montgomeryschools.org እና www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/. ስለ ልጅዎ ትምህርት ቤት መረጃ ለማግኘት ይህንን በይነመረብ ይክፈቱ እና Schools የሚለውን ከፍተው ያንብቡ፦ www.montgomeryschools.org

### የክትባት መስፈርቶች

2025-2026 የትምህርት አመት 7ኛ ክፍል የሚገቡ ወይም ለ MCPS አዲስ የሆኑ እና ከ 8ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የሚገቡ ተማሪዎች ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በፊት አንድ ዙር የቴታነስ-ዲፍቴሪያ-አሴሉላር ፐርቱሲስ/Tetanus-diphtheria-acellular pertussis (Tdap) ክትባት እና አንድ ዙር የሜኒንጎኮካል ኮንጁጌት/Meningococcal conjugate (MCV4) ክትባት የወሰዱ መሆን አለባቸው። ትምህርት በጀመሩ በ 20 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ የክትባቶች ማስረጃ ያላቀረቡ ተማሪዎች የክትባት ማረጋገጫን በሚመለከት፣ ገና ያልተረጋገጠ ፖዚቲቭ ውጤት ወይም የክትባት ቀጠሮ የተያዘበት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው። በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ቤት ለመከታተል እነዚህን ክትባቶች መውሰድ አስፈላጊ መስፈርት ነው። ተቀባይነት ያላቸው የክትባት ማስረጃዎች ከተማሪው(ዋ) የጤና ባለሙያ ወይም ከሜሪላንድ የጤና ጥበቃ ዲፓርትመንት የክትባት ማዕከል የተሰጠ ሰርተፊኬት (ቅጽ 896) በጤና ባለሙያ ተሞልቶ ከኮምፒዩተር የታተመ የክትባት ማስረጃ ነው። ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/mdh_896_form.pdf። ስለ ክትባት መስፈርቶች ተጨማሪ መረጃ እዚህ ይገኛል፦ https://health.maryland.gov/phpa/OIDEOR/IMMUN/pages/back-to-school-immunization-requirements.aspx

## የፌርጀ ብዙ ስርዓተ ትምህርት ኃላፊነትና ተጠያቂነት/ አካውንቴቢሊቲ

- በሜሪላንድ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ዘርፍ ለተሟላ ሥርዓተ ትምህርት፣ ከትምህርት ቤት አጠቃላይ የሪፖርት ካርድ ውጤት 10 በመቶውን ይይዛል። ይህ ማለት ትምህርት ቤቶችን እና ዲስትሪክቶችን በሚገባ የተጠናከረ የኮርስ አቅርቦት እንዲኖራቸው እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የእነዚህ ኮርሶች ተደራሽነት ኖሯቸው መመዝገባቸውን የማረጋገጥ ተጠያቂነት አለባቸው።
- ትርጉሙ:- ይህ በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማእቀፍ (ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል) በስነ ጥበብ፣ የአካል ማጎልመሻ ትምህርት፣ የጤና፣ እና የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት አስተሳሰብን በመገንባት ረገድ ቢያንስ በማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የተመዘገቡትን ኮርስ በመቶኛ ይይዛል። MSDE አሁን ያለው ትርጓሜ አንድ ተማሪ 6ኛ፣ 7ኛ ወይም 8ኛ ክፍል እያለ(ች) ከእነዚህ የፀደቁ ኮርሶች በማንኛውም ከተመዘገበ(ች)/ ከተማረ(ች) ተማሪው(ዋ) መስፈርቱን ያሟላል/ታሟላለች። እነዚህ ኮርሶች ሙሉ ዓመት፣ ሴሚስተር፣ እና ሩብ ዓመት "በማፈራረቅ" የሚሰጡ ኮርሶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ሁሉም ክሬዲት የሚያስገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች ለአንድ አመት ጊዜ መወሰድ አለባቸው።
- ስነ ጥበብ እና የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት መስፈርቶች በተመረጡ የኮርስ አማራጮች መሟላት አለባቸው። የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት እና በስነ ጥበብ ዘርፍ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ኮርሶች ዝርዝር እዚህ ይገኛል፡ Computational Thinking School Year 2024–2025 ESSA Accountability Approval List። ማሳሰቢያ:- የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ኮርሶች የኮምፒውተር ሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ ትምህርት እና የምህንድስና ኮርሶችን ያካትታሉ።
- የሚከተሉት የ 6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎችን እቅድ ማውጫ እና መርሐግብር ለማዘጋጀት ዓላማ እንደ ግብዓት ሊያገለግሉ ይችላሉ።

| 6ኛ ክፍል የሚያስፈልጉ ኮርሶች | 7ኛ ክፍል የሚያስፈልጉ ኮርሶች | 8ኛ ክፍል የሚያስፈልጉ ኮርሶች |
|---|---|---|
| እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ ኮርስ<br>ሌላ ተመራጭ ኮርስ(ሶች) (ሙሉ ዓመት፣ ሴሚስተር፣ ወይም ሩብ አመት በማፈራረቅ) | እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ ኮርስ<br>ሌላ ተመራጭ ኮርስ(ሶች) (ሙሉ ዓመት፣ የሴሚስተር ወይም የሩብ አመት በማፈራረቅ) | እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ ኮርስ<br>ሌላ ተመራጭ ኮርስ(ሶች) (ሙሉ ዓመት፣ የሴሚስተር ወይም የሩብ አመት በማፈራረቅ) |
| ሁለገብ የተሟላ ሥርዓተ ትምህርት ያስፈልጋል | | |
| ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የተመረጡ የስነጥበብ (ፋይን አርትስ) ኮርሶች "Fine Arts and Computational Thinking/የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት" በሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች ሪፖርት ካርድ ላይ ክሬዲት ይሰጣል። Fine Arts ኮርሶች ውስጥ የሚገኙ ኮርሶችን ይመልከቱ። | | |

## የተማሪ እቅድ አወጣጥ ናሙና

ትምህርት ቤቶች ከተማሪዎች ግለሰባዊ ፍላጎቶች እና ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ለሚያቀርቡት ትምህርት እና የመርሃግብር ተሞክሮዎችን ለመንደፍ እነዚህ እቅድ ማዘጋጃዎች እንደ ናሙና ቀርበዋል።

| ተማሪ A:-<br>መደበኛ/ተለምዷዊ የተመራጭ ኮርሶችዳሰሳ | ተማሪ B:-<br>ዓመት የሚቆይ የእይታ ወይም የትወና ኪነጥበብ ትምህርት ምዝገባ | ተማሪ C:-<br>አመት የሚማሩት STEM/የኮምፒውተር ሳይንስ ምዝገባ |
|---|---|---|
| እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ/ድጋፍ<br>"ስነ ጥበብ/Fine Arts ወይም Computational Thinking/የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት" ኮርሶች በዓመት፣ በሴሚስተር ወይም በሩብ አመት ፈረቃ ይወሰዳሉ። | እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>ውስብስብ ፕሮብሌሞችን የመፍታት የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት አስተሳሰብ<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ/ድጋፍ<br>ሙሉ ዓመት የዳንስ፣ ኮራል ሙዚቃ፣ አጠቃላይ ሙዚቃ፣ የሙዚቃ መሣሪያዎች፣ የሚዲያ አርት፣ ቲያትር ወይም ቪዥዋል አርት | እንግሊዝኛ ወይም ELD<br>ሂሳብ<br>ሳይንስ<br>የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ<br>የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት/ጤና<br>ስነ ጥበብ/Fine Arts<br>የዓለም ቋንቋ ወይም ተመራጭ/ድጋፍ<br>ሙሉ ዓመት የሚማሩት STEM፣ የኮምፒውተር ሳይንስ፣ ወይም ምህንድስና |

*ማሳሰቢያ:-*

- የቀረቡት የተማሪ ናሙናዎች ለተማሪዎች ሰፊ አማራጮችን እና የተሟላ ሥርዓተ ትምህርት እንደሚሰጥ ማረጋገጫ ምሣሌዎች ናቸው። የሩብ አመት ወይም የሴሚስተር አማራጮች ማንኛውንም የአንድ አመት ኮርስ መተካት የለባቸውም።
- የሚከተሉት ኮርሶች "ስነ ጥበብ/Fine Arts እና Computational/የስሌት አስተሳሰብ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት ነው። ተማሪዎች መስፈርቱን ለማሟላት የሙሉ አመት ኮርስ ማጠናቀቅ አለባቸው።

## አጠቃላይ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራም

የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራም የተነደፈው በብሔራዊ፣ በስቴት እና በአካባቢ ደረጃ በተደነገጉ መመሪያዎች መሠረት በአምስቱ የተማሪዎች እድገት ዘርፎች (አካዳሚክ፣ የሥራ ሙያ፣ የግል፣ የእርስበርስ ጤናማ እድገት) የእያንዳንዱን ተማሪ አካዴሚያዊ ስኬት እና ግላዊ እድገት ከፍ ለማድረግ ነው። በሁለገብ የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራም፣ እያንዳንዱ ካውንስለር ከት/ቤት ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ማህበረሰብ ጋር የቡድን አባል በመሆን ወጣት ታዳጊዎች የአካዳሚክ ስኬት የሚያገኙበት ምቹ የትምህርት ቤት አውድ እና ድባብ ለመፍጠር ይሰራል/ትሠራለች። የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች የተነደፉት ተማሪዎች ጥሩ ግላዊ እድገት እንዲኖራቸው፣ አወንታዊ ማህበራዊ ክህሎቶችን እና እሴቶችን እንዲያዳብሩ፣ ተገቢ የስራ ግቦችን እንዲተልሙ እና በአካዳሚክ ውጤታማ የሆኑ የአለም ማህበረሰብ አባላትን እንዲያበረክቱ ለመርዳት ነው።

## የትምህርት ቤት ካውንስሊንግ ሥርአተ ትምህርት

K–12 ካውንስለሮች የማማከር ፕሮግራምን—ተግባራዊ ያደርጋሉ

- የአካዳሚክ ችሎታ እንዲያዳብሩ ድጋፍ መስጠት
- ድርጅታዊ፣ የማጥናት፣ እና ፈተና-የመውሰድ ችሎታ እንዲያበለጽጉ መርዳት
- ራስን እና ሌሎችን የመረዳት ትምህርት መስጠት
- የአቻ ግንኙነትን እና ውጤታማ ማህበራዊ ክህሎቶችን ማዳበር
- ግንኙነት፣ ችግር መፍታት፣ ውሳኔ መስጠት እና የግጭት አፈታት ዘዴ
- የሥራ ሙያ ግንዛቤ፣ ቅኝት እና እቅድ መተለም
- የተለያዩ ባህሎች ብዝሃነት ግንዛቤ

ግላዊ የተማሪ እቅድ ዝግጅት

- ግብ መተለም/ውሳኔ መስጠት
- የትምህርት እቅድ ዝግጅት
- የሙያ ሥራ እቅድ ዝግጅት
- ጥንካሬን፣ ድክመቶችን እና ራስን የመምራት ችሎታን ጭምር ራስን የመገንዘብ ትምህርት
- የሽግግር እቅድ መተለም

ምላሽ ሰጪ አገልግሎቶች

- የግለሰብ እና የአነስተኛ-ቡድን ካውንስሊንግ
- የግለሰብ/የቤተሰብ/የትምህርት ቤት ቀውስ ሲከሰት ጣልቃገብነት
- የእኩዮች ቅንብር
- ካውንስሊንግ፣ ምክር/ትብብር
- ማጣቀሻዎች

የሲስተም ድጋፍ

- ሙያ ማዳበር
- ካውንስሊንግ፣ ምክር፣ትብብር፣ እና መቧደን
- ፕሮግራም ማኔጅመንት እና ትግበራ

## ትምህርት ላይ መገኘት/መከታተል

ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለማግኘት በተማሪዎች እና በወላጆች/በአሳዳጊዎች በኩል ትምህርት ቤት ለመገኘት እና ለመከታተል ቁርጠኝነት መኖሩ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ(ዷ) ተማሪ ትምህርቱ(ቷ)ን በመደበኛነት እንደሚከታተል/እንደምትከታተል ለማረጋገጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የት/ቤት ሰራተኞች የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች ሁሉንም መርሃግብር የተያዘላቸውን ትምህርቶች እና የጸደቁ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን/አክቲቪቲዎችን መከታተል አለባቸው፤ እና ሁሉንም የተመደበላቸውን የትምህርት ስራ በሰዓቱ/በጊዜው የማጠናቀቅ ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በሙሉ ቀን ፕሮግራም መመዝገብ ወይም በወላጅ/አሳዳጊ እና በርእሰ መምህር በተፈቀደላቸው አማራጭ ፕሮግራም ወይም ተግባር ላይ ተመጣጣኝ ጊዜ ማሳለፍ አለባቸው። MCPS ደንብ JEA-RA, የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት/መከታተል, at ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jeara.pdf.

## የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት ማድረግ

የትምህርት ቦርድ ለሁሉም ተማሪዎች ጥብቅ የትምህርት ስራ አፈጻጸም እና ስኬታማ የውጤት ደረጃዎችን ለማስጠበቅ፣ የተማሪዎችን የትምህርት እድገት ለመገምገም እና ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎች ለመረዳት የሚችሉት ለትምህርት ዓላማዎች ተስማሚ የሆነ አሠራር ለማዳበር ቁርጠኛ ነው። የቦርድ ፖሊሲ IKA, የትምህርት ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/ikara.pdf), እና በተጨማሪ MCPS ደንብ IKA-RA, ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ (www.montgomeryschoolsmd.org/department/policy/pdf/ikara.pdf)ተጠባቂ ነገሮች እና መመሪያዎች የስርአተ ትምህርት እና የማስተማር ፕሮግራሞች ተባባሪ ሱፐርኢንቴንደንት ቢሮ በዚህ ድረገጽ ላይ የአሠራር ሂደቶችን መግለጫ ያወጣል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/ikara.pdf

## የትምህርት ውጤት አሰጣጥ ሒደት

የውጤት አሰጣጥ ሂደት በትምህርት ቤቶች መካከል ወጥ በሆነ አሠራር ይተገበራል። የውጤት አሰጣጥ ተግባር ግልጽ እና ወቅቱን ጠብቆ የሚሰጥ፣ ከስርአተ ትምህርቱ ጋር የተሣለጠ፣ የተማሪዎች አካደሚክ ስኬት ትክክለኛ ነጸብራቅ እና የተማሪዎችን አፈጻጸም ፍትሃዊነት በአግባቡ መግለጽ አለባቸው። የውጤት አሰጣጥ ፍትሃዊ መሆን እና ለማከናወን የሚቻል፣ እንዲሁም ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን የሚደግፉ መሆን አለባቸው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ እንደተገለጸው በሪፖርት ካርዶች ላይ ያሉ ውጤቶች ከተማሩት ኮርስ የሚጠበቅ የትምህርት ስኬትን ያንፀባርቃሉ። ተጨማሪ ክሬዲት መጠቀም ተግባራዊ አይሆንም። የትምህርት አመት መጀመሪያ ላይ ስለ ኮርስ አተገባበር እና የውጤት አሰጣጥ ሂደቶች፣ እና ተግባራዊ የሚደረጉ ወጥነት ያላቸው አሠራሮች ለተማሪዎች እና ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች በሴሚስተር መጀመሪያ ላይ በግልፅ በጽሑፍ ይሰጣቸዋል። ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ ተጨማሪ መረጃ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/ikara.pdf.

## የቤት ሥራ

በአጠቃላይ የተማሪ ፕሮግራም ውስጥ የቤት ስራ አስፈላጊ ተግባር ነው። መምህራን ከስርአተ ትምህርቱ ጋር የተያያዙ የቤት ስራዎችን ይሰጣሉ። ሁለት አይነት የቤት ስራ ምድቦች አሉ፡- እንደ መምህሩ የውጤት አሰጣጥ ምደባ እና የትምህርት ግቦች ላይ በመመርኮዝ የቤት ስራ/Homework 90% ወይም 10% የውጤት ምድብ ሊኖራቸው ይችላል።



በሁለቱም የቤት ስራ ዘርፎች ላይ ወቅታዊ እና ትርጉም ያለው አስተያየት የሚሰጥበት ሲሆን የተለያዩ ቅርጾች ሊኖሩት ይችላል። ይህን ድረገጽ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/info/grading/SEC_HomeworkProcedures.pdf.

## ዲስትሪክት አቀፍ ምዘናዎች

በዲስትሪክት አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ ምዘናዎች የትምህርት ብቃት ማረጋገጫው አንድ አካል ናቸው።

- በተለይ በተመደበ ጊዜ ውስጥ፣ ለተለየ የክፍል ደረጃ፣ እና የተለየ የመካከለኛ እና የሁ/ደ/ት/ቤት ኮርሶችን መመዘኛ ለመስጠት ዲስትሪክት አቀፍ ምዘና ያስፈልጋል።

## የተማሪ አካደሚያዊ እድገትን ሪፖርት ማድረግ

መምህራን በማርክ መስጫ ወቅት ለተማሪዎች እና ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ስለ አካደሚያዊ ስኬት መረጃ ይሰጣሉ። ይህ ግብረመልስ የሚከተሉትን ጨምሮ በርካታ ቅርጾች ሊኖሩት ይችላል፡-

- ሪፖርት ካርዶች
- በመሃል ያለ ጊዜ/የአጭር ጊዜ/የአካደሚክ እድገት ሪፖርቶች
- የኦንላይን ትምህርት የውጤት ሪፖርቶች
- የወላጅ/አሳዳጊ ኮንፈረንስ
- መደበኛ ያልሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች
- የአስተማሪ ግብረመልስ

## የትምህርት ቤት ቤተ መፃህፍት/ላይብራሪ የሚዲያ ፕሮግራም

በትምህርት ቤት ቤተ መፃህፍት የሚዲያ ፕሮግራም ክፍል መጀመሪያ ላይ በዚህ ዓረፍተ ነገር ጀምር(ሪ)፡- የት/ቤት ቤተ መፃህፍት የሚዲያ ፕሮግራሞች ተልእኮ ጸረ-ዘረኝነት እና ፀረ-አድሎአዊነት የመረጃ ሊተርሲ ትምህርትን ማሳደግ ሲሆን ተማሪዎች የስነፅሁፍ ፍቅር እንዲያዳብሩ እና በኮሌጅ እና በስራ ግቦቻቸው እንዲሳካላቸው የሚያስችላቸውን ፍትሃዊ የመገልገያ/ሪሶርስ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ነው።

እንደ መምህር እና ተባባሪ በመሆን፣ የት/ቤት ቤተመፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች ተማሪዎችን ለማንበብ፣ ለመገምገም፣ የህትመት እና የዲጂታል ግብዓቶችን በብቃት ለመጠቀም አስፈላጊውን እውቀት እና ክህሎት ለማስታጠቅ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ቤተ መፃህፍት የሚዲያ መርሃ ግብር በመረጃ ሊተርሲ እና በዲጂታል ዜግነት ላይ ትምህርት በመስጠት፣ አሳታፊ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት እና በተከታታይ መረጃዎችን በመሰብሰብ የተማሪዎችን ስኬት በማጎልበት ላይ ያተኮረ ነው።

ጠንካራ የትምህርት ቤት ቤተመፃህፍት የሚዲያ ፕሮግራም መርሆዎች፡-

- ሊተርሲ እና የስኬት ድጋፍ፡- የት/ቤት ቤተመፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች የስነፅሁፍ ፍቅርን በማስተዋወቅ እና ተማሪዎችን በግላቸው አካዳሚያዊ የምርምር ፍላጎቶቻቸውን በመርዳት ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ።
- የማስተማር አጋርነት፡- የትምህርት ባለሙያዎች እና የማስተማር አጋሮች እንደመሆናቸው መጠን፣ የቤተ መፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች ከኮሌጅ እና ከስራ ዝግጁነት (CCR) መመዘኛዎች ጋር የተጣጣሙ ፕሮጀክቶች ላይ ያተኮሩ የመረጃ ሊተርሲ ችሎታዎችን ለማዳበር ከመምህራን ጋር ይተባበራሉ። ይህ ሥርዓተ ትምህርት ሂሳዊ አስተሳሰብን እና የምርምር ክህሎቶችን በተግባራዊ የመማር ልምድ ያዳብራል።
- የፈጠራ (ኢኖቬቲቭ) ትምህርት አውድ፡- የትምህርት ቤት ቤተ-መጻሕፍት ተግባራዊ፣ ልምድ የሚቀሰምባቸው፣ እና አሳታፊ የመማር እድሎችን በሚሰጡ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የተደራጁ ናቸው። እነዚህ ቦታዎች ፈጠራን ለማነሳሳት እና በተማሪዎች መካከል ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት" ችግር ፈቺ ስልቶችን ለማዳበር የተነደፉ ናቸው።
- ፍትሃዊነት እና የብዝሃነት ውክልና፡- የቤተ መፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች ፍትሃዊነትን፣ ተደራሽነትን፣ እና የተለያየ ዝሃነት ውክልናን ከማረጋገጥ አንፃር አጠቃላይ አካላዊ እና ዲጂታል ስብስቦችን የመገንባት እውቀታቸውን ይጠቀማሉ። ይህ ቁርጠኝነት ሁሉም ተማሪዎች እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ሁሉንም አካታች የትምህርት መርጃ ግብዓቶችን እንዲያገኙ ያግዛል።
- የማህበረሰብ ተሳትፎ፡- ቤተ መፃህፍቱ የትምህርት ቤት ማዕከል/ልብ/ ሆኖ ያገለግላል። የቤተ መፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች፥ ወላጆች/ ተንከባካቢዎች የማህበረሰብ ሪሶርሶችን የተማሪዎችን ስኬት ለማዳበር እና የማህበረሰብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር በትብብር እንዲሰሩ የሚያስችል ልዩ ሚና አላቸው።

የቤተ መፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች ተማሪዎች የህትመት እና የዲጂታል ግብዓቶችን በብቃት እና በስነምግባር መጠቀማቸውን ማረጋገጥ አለባቸው። ተማሪዎች በተለያየ ቅርጸት (ኢ-ቡክስ፣ በምንባብ የሚደመጡ መጽሐፍት/ኦዲዮ መጽሐፍት፣ በኅትመት፣ በግራፊክ ልቦለድ፣ በትላልቅ ኅትመት፣ በኤሌክትሮኒክስ ዳታቤዝ፣ ወዘተ) በተለያዩ ጽሑፎች እና መረጃዎች ላይ ለማሳተፍ እንዲያመች የትምህርት መርጃዎችን በማዘጋጀት የትምህርት ልምዳቸውን ያበለጽጋሉ። በተጨማሪም ቤተ መፃህፍት ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች በእነዚህ መገልገያዎች/ሪሶርሶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ያቀርባል። በተጨማሪም፣ የሚዲያ ስፔሻሊስቶች ስለ ተደራሽነት፣ ስለ ግላዊነት፣ ስለ ዲጂታል አጠቃቀም ስነምግባር፣ እና ስለ ቅጂ መብት አከባበር መመሪያ ይሰጣሉ።

የቤተ መፃህፍት ሚዲያ ስፔሻሊስቶች ከክፍል አስተማሪዎች ጋር በመተባበር የመረጃ ሊተርሲ መርጃዎችን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዋሃድ የትምህርት ልምድን ከተዛማጅ እና ትክክለኛ ይዘት ጋር ያበለጽጋሉ። በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የዲጂታል ዜግነት መሪ በመሆን፣ እንደ ተባባሪ መምህር፣ ተማሪዎችን በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች በመደገፍ እና የዲጂታል ዜግነት ልምዶችን በማካፈል- አስተማማኝ የመረጃ ፍለጋ እና ማጋራት በመሳሰሉ ተግባራት 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ሰፋ ያሉ ትምህርቶችን በማካተት ያገለግላሉ።

MCPS በት/ቤቶቻችን ቤተ መፃህፍት ፕሮግራሞች ውስጥ ንቁ፣ አካታች፣ እና አዳዲስ የመማሪያ አውድ ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው። ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ከትምህርት ቤትዎ ቤተ-መጽሐፍት ጋር እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን የሚዲያ ባለሙያ ያነጋግሩ።

## የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ የሚከናወነው የተማሪዎች የአገልግሎት ትምህርት (SSL) ፕሮግራም የተማሪዎች የአገልግሎት ባህልን እና የዜግነት ተሳትፎን በሚመለከት ተማሪዎች ሃላፊነት እንዲሰማቸው ያበረታታል። በሜሪላንድ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት የመመረቂያ መስፈርት ነው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ለመመረቅ ቢያንስ 75 የአገልግሎት ትምህርት ሰአት ማጠናቀቅ አለባቸው። ይህንን መስፈርት 5ኛ ክፍል ጀምሮ በሠመር ወቅት ለማሟላት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ድረስ SSL ሰዓቶችን ማጠራቀም ይችላሉ። በሲንየር አመታቸው ኤፕሪል ወር የመጀመሪያው አርብ ድረስ 240 ወይም ከዚያ በላይ SSL ሰአት ያገኙ ተማሪዎች የክብር አገልግሎት ሰርተፍኬት ይሰጣቸዋል። በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ዓመት በኤፕሪል ወር የመጀመሪያ አርብ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) 75 ሰአት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በዚያው አመት የሱፐርኢንቴንደንት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሽልማት ያገኛሉ። ዝግጅት፣ ተግባር እና እውቀታቸውን በተግባር ማንፀባረቅ የተማሪ አገልግሎት ትምህርትን (SSL) ከተለምዷዊ የበጎ ፈቃደኝነት እና የማህበረሰብ-አገልግሎት ጥረቶች የሚለዩት ሦስቱ የአገልግሎት ትምህርት ደረጃዎች ናቸው።

የአገልግሎት ትምህርት ሰአት የሚገኘው በሚከተለው ሁኔታ ነው።

- የትምህርት ቤት ኮርሶች—በዚህ የኮርስ መጽሔት ውስጥ የተዘረዘሩትን የተወሰኑ ኮርሶች በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ፣እና ሶስቱን የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) አላማዎች ማሟላት።
- የትምህርት ቤት ክለቦች—በትምህርት ቤት በሚደገፉ ክለቦች እና ድርጅቶች የአገልግሎት ተግባራት ውስጥ ሦስቱን የአገልግሎት ደረጃዎች ሙሉ በሙሉ መሳተፍ እና ማጠናቀቅ።
- የማህበረሰብ ድርጅቶች እና የአገልግሎት እድሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (MCPS SSL) መመሪያዎችን ማሟላት አለባቸው።—የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (MCPS SSL) መመሪያዎችን በመከተል ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ እድል ለማግኘት MCPS - SSL ድረ ገጽ ላይ ያሉትን ድርጅቶች ዝርዝር ይመልከቱ፡- www. mcps-ssl. org። MCPS የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እድሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃደኝነት ማእከል (MCVC) ድረ-ገጽ ላይ MCPS SSL ምልክት ስላለበት ተለይቶ ይታወቃል www.montgomeryserves.org ተማሪዎች MCPS ቅጽ 560-50 በመሙላት በተናጠል የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ጥያቄን በማቅረብ ሌሎች የአገልግሎት ትምህርት ዓይነት እንዲፈቀድላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

በአካል የሚደረግ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰአታት በሙሉ በህዝባዊ አገልግሎት መስጫዎች ቦታ መሆን አለባቸው፣ በባህሪያቸው መንፈሳዊ ያልሆነ አገልግሎት መስጠት እና ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ከቀረጥ ነፃ በሆነ ድርጅት ሆኖ በአዋቂ ተወካይ ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል። ተማሪዎች ህጋዊ ፈቃድ ባለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይም በ MCPS ሰራተኛ ድጋፍ በሚካሄድ ቨርቹዋል/የርቀት SSL እድሎች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ዘመዶች በዚህ ተግባር ላይ ተማሪን በቀጥታ መቆጣጠር አይችሉም። አንድ SSL ሰአት የሚሰጠው ከትምህርት ቀን ውጭ ለሚሰጥ ለእያንዳንዱ የአንድ ሰአት አገልግሎት ሲሆን በ 24 ሰአት ውስጥ ቢበዛ 8 ሰአት ብቻ መሆን አለበት። MCPS ቅጽ 560-51፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት እንቅስቃሴ ማረጋገጫ፣ ሁሉም የተማሪ አገልግሎት የተሰጠባቸው (SSL) ሰአቶቹ መመዝገብ አለባቸው። SSL FAQs ዘወትር የሚጠየቁ ጥያቄዎች እና ተጨማሪ መረጃዎች MCPS SSL www.mcps-ssl.org እና MCVC ድረ ገጽ www.montgomeryserves. orgይመልከቱ። በተናጠል የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ለመጠየቅ፣ እባክዎ ማንኛውንም የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም የሁ/ደ/ት/ቤት SSL አስተባባሪ ያነጋግሩ። (https://bit.ly/SSLCoordinatorsMS ወይም https://bit.ly/SSLCoordinatorsHS)

## ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሁ/ደ/ት/ቤት ክሬዲት

በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ኮርሶች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይ ይካተታሉ፣ ነገር ግን የክፍል ውጤቶቹ ድምር GPA ስሌት ውስጥ አይገቡም። በእያንዳንዱ ሴሚስተር መጨረሻ ላይ በኦቶሜትድ በሚሰራ ሂደት የትኞዎቹን ኮርሶች ማካተት ወይም መወገድ እንዳለበት ይወስናል። ትራንስክሪፕቶች እና የተማሪ ውጤት እና የመመረቂያ ክሬዲት ሪፖርት (SGGCR) ከፌብሩዋሪ አጋማሽ በኋላ ይህን GPA ያንፀባርቃሉ።

ስለ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የውጤት አሰጣጥ ተጨማሪ መረጃ እዚህ ማግኘት ይቻላል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/grading/report-cardssecondary.aspx.

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በእያንዳንዱ ሴሚስተር የመጨረሻ ክፍል A፣ B፣ C ወይም D በማግኘት ከሁ/ደ/ት/ቤት ተማሪዎች ጋር ተመሳሳይ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። ተጨማሪ መረጃ MCPS ደንብ IKC-RA፣ አማካይ የውጤት ነጥብ (GPA) እና አማካይ የድምር ውጤት ነጥብ (WGPA)፣በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/ikcra.pdf

## የሜሪላንድ ትምህርት ቤት አጠቃላይ የግምገማ ፕሮግራም

የሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም (MCAP) ለተወሰኑ ኮርሶች የይዘት መመዘኛዎች በተቀመጠው መስፈርት መሰረት የተማሪዎችን የትምህርት ችሎታ እና እውቀት ለመመዘን የተዘጋጁ ወይም MSDE ተቀባይነት ያላቸው ፈተናዎችን ያካትታል። የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘናዎች (MCAs) 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ/ሊተርሲ እንዲሁም 8ኛ ክፍል ሂሳብ፣ሳይንስ እና ማህበራዊ ጥናትን በተመለከተ በስቴት እና በፌደራል የተደነገጉ ምዘናዎች ናቸው። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት አልጀብራ 1 MCAP የወሰደ(ች) ተማሪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መመረቂያ መስፈርቱን ያሟላል። ተማሪዎች የሚመለከታቸውን ኮርሶች ከጨረሱ በኋላ እነዚህን መመዘኛዎች ይወስዳሉ። MCAP ለተወሰኑ ተማሪዎች አማራጭ ምዘናዎችንም ያካትታል።

የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና ከ 2023–2024 ጀምሮ፣ሳይንስ እና ስነ-መንግስት የተማሪን የመጨረሻ ውጤት 20 በመቶ ይይዛል።

| የሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም (MCAP)<br>እነዚህ የምዘና መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) | |
|---|---|
| አልጄብራ 1 | በአልጄብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• የአልጀብራ 1 ምዘና መውሰድ |
| እንግሊዝኛ 10 | በእንግሊዝኛ ኮርስ የተገኘ 10 ክሬዲት ወይም ተመጣጣኝ፣ ወይም እንግሊዝኛ EMLs 10 እና<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት/ሊተርሲ ምዘና መውሰድ |
| ስነ መንግስት | ብሔራዊ፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ስነ መንግስት ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ ክሬዲት እና<br>• ስነ መንግስት የመጨረሻ ኮርስ (EOC) ፈተና መውሰድ። EOC የብሔራዊ፣ የስቴት እና የአካባቢያዊ (NSL) ስነመንግስት ሴሚስተር B 20% ይይዛል። የ AP ስነ መንግስት ተማሪዎች AP ስነ መንግስት ፈተና ወይም MCAP ስነ መንግስት EOC ምዘና መውሰድ አለባቸው። |
| ሳይንስ | በባዮሎጂ ወይም በሌላ ተመጣጣኝ ኮርስ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• ስነ ህይወት/ላይፍ ሳይንስ (EOC) የመጨረሻ ኮርስ ግምገማ መውሰድ። EOC ባዮሎጂ ሴሚስተር B ውጤት 20% ይይዛል። AP ባዮሎጂ ተማሪዎች የባዮሎጂ EOC ምዘና መውሰድ አለባቸው። |

[1]የማሟያ ፈተና፡- በማሟያ ፈተናዎች (AP/IB) ብቁ የሚያደርጋቸው ነጥቦችን ያገኙ ተማሪዎች በዚያ ትምህርት MCAP መስፈርት ያሟላሉ።

[2] ክሬዲት ማስተላለፍ: ከሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ውጪ በዝውውር የሚመጡ ተማሪዎች አንዳንድ የ MCAP መስፈርቶችን ሲዛወሩ ባላቸው ክሬዲት ማሟላት ይችሉ ይሆናል።

ስለ MCPS የመመረቂያ መስፈርቶችን በተመለከተ ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/graduation-requirements.aspx።

## እንግሊዘኛ ቋንቋ ማዳበር (ELD)

እንግሊዘኛ ለመማር እርዳታ የሚያስፈልጋቸው እያደገ ያለ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት (ELP) የስቴት ሥርዓተ ትምህርት (MSDE) ጋር የተሣለጠ ትምህርት ያገኛሉ። ተማሪዎች በቋንቋ ፍላጎታቸው መሰረት በቡድን ተመድበው ይማራሉ።

## ውስን እና መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ያቋረጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ውስን እና መደበኛ ትምህርት (ሁለተኛ ደረጃ SLIFE) ፕሮግራም ያቋረጡ ወይም በተስተጓጎለ ትምህርት ምክንያት ውስን የሆነ ወይም ከዚህ በፊት ምንም አይነት ትምህርት ወይም ጉልህ የሆነ ትምህርት ያልነበራቸውን EMLs የቋንቋ እና የአካዳሚክ ፍላጎቶችን ለማሟላት የተነደፈ ፕሮግራም ነው። SLIFE ፕሮግራም

ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃትን እና መሰረታዊ ሊተርሲ እና የአካዳሚክ ክህሎትን የማዳበር ትምህርት ያገኛሉ። እነዚህ EMLs ለአካዳሚክ እና የማህበራዊ ትምህርት ቤት ድባብ ጋር እንዲለማመዱ ለማመቻቸት ትምህርት እና ድጋፍ ያገኛሉ። SLIFE ፕሮግራም በተመረጡ የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሰጣል።

## ልዩ ትምህርት ማስተማር

ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ያለው/ያላት ተማሪ፣ ወደ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሻገር-ስትሻገር እየወሰደ(ች) ያለውን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ማግኘቱ(ቷ) ይቀጥላል። ተማሪዎች ክህሎታቸውን ለማዳበር እና እውቀት ለማግኘት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በተለያዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴሎች ትምህርት ሊያገኙ ይችላሉ። የአገልግሎት ዘርፎቹ ስለ ትምህርቱ ከልዩ ትምህርት ባለሙያዎች ጋር ምክክር ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም፤ በአጠቃላይ ትምህርት ክፍል ቀጥተኛ አገልግሎት ስለመስጠት፣ ከሪሶርስ ክፍል በማውጣት ለብቻ የልዩ ትምህርት ክፍል ውስጥ ቀጥተኛ አገልግሎት ማግኘት፣ ወይም አንዳንድ ከላይ የተጠቀሱትን በጥምረት አገልግሎት መስጠትን የሚያካትት ቢሆንም ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

ልጅዎ ትምህርት የመቅሰም እክል ካለበ(ባ)ት እና ግምገማ ሊያስፈልግ ይችላል ብለው ከተጠራጠሩ፣ እባክዎን መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ያነጋግሩ።

## የሴክሽን 504 ፕላን Section 504 Plan

የአካል ጉዳተኛ ተማሪ የአካል ወይም የአዕምሮ እክል ካለበ(ባ)ት እና አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን የሚገድብ ከሆነ የተሃድሶ ህግ 1973 ሰክሽን 504 መሰረት የአኮሞዴሽንስ አገልግሎቶችን ለማግኘት ብቁ ሊሆን ይችላል/ብቁ ልትሆን ትችላለች። አንድን ተማሪ ሰክሽን 504 ብቁ መሆኑ(ኗ)ን ለማረጋገጥ መምህራን ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች ግምገማ እንዲደረግ ሊጠይቁ ይችላሉ። ሰክሽን 504 ስር አኮሞዴሽን ለማግኘት የብቁነት መስፈርት የሚያሟላ እያንዳንዱ ተማሪ በትምህርት ቤቱ የተዘጋጀ ሰክሽን 504 እቅድ ይኖረዋል/ይኖራታል። ለበለጠ መረጃ እባክዎን ይህን MCPS ድረ ገጽ ይጎብኙ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/studentservices/Section-504/ ወይም ሴክሽን 504 አስተባባሪ በስልክ ቁጥር 240-987-8031 ያነጋግሩ።

## አማራጭ ፕሮግራሞች

እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በትምህርት ቤት ደረጃ የተመሰረተ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ለማዘጋጀት እና ለመተግበር ሰራተኞች አሉት። ይህ ፕሮግራም ለተማሪዎች ቀጥተኛ አካዳሚያዊ፣ ማህበራዊ ስሜታዊ እና የባህሪ-አያያዝ አገልግሎቶችን ይሰጣል እንዲሁም ለሰራተኞች ድጋፍ ይሰጣል። ቀጣይነት ባለው መመሪያ እና ክትትል፣ በእነዚህ ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የበለጠ ስኬትን ማግኘት እና በትምህርት ቤት ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ መቆየት አለባቸው።

## ኢንተርናሽናል ባካሎሬት የመካከለኛ ዓመት ፕሮግራም

የመካከለኛ አመት ፕሮግራም (MYP) 11 እስከ 16 ዓመት እድሜ ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች በፈጠራ ላይ እንዲያተኩሩ፣ በጥልቀት እንዲያስቡ እና አሳቢያቸውን የሚያጋሩ እንዲሆኑ የሚያበረታታ የትምህርት ማዕቀፍ ይሰጣል። MYP ተማሪዎች መደበኛ ትምህርታቸውን ከገሃዱ አለም ጋር በማገናኘት እንዲያገናዝቡና እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ በማበረታታት አእምሯቸውን እንዲያበለፅጉ አፅንዖት ይሰጣል። ለወጣቶች አለምአቀፍ መሪዎች እንዲሆኑ አስፈላጊ ባህሪያትን—የኮሙኒኬሽን፣ የባህል ብዝሃነትን መረዳትና መግባባት እና አለም አቀፍ ተሳትፎ የማድረግ ክህሎት ማዳበርን ያበረታታል። ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዘርፎች፣ ሂሳዊና በጥልቀት የማሰብ ችሎታ በማዳበር እና በመተግበር በጥናት ላይ ይሳተፋሉ እንዲሁም ሁለተኛ ቋንቋ ያጠናሉ። MYP በአሁኑ ጊዜ በኒውፖርት ሚል፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ኢንተርናሽናል፣ ጁሊየስ ዌስት፣ ዌስትላንድ፣ ፍራንሲስ ስኮት ኪይ፣ ሞንትጎመሪ ቪሌጅ፣ ኔልሰቪል፣ ሲልቨር ክሪክ፣ ሮቤርቶ W. ክለመንተ እና ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ Jr መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ እንደ ሙሉ የትምህርት ቤት ፕሮግራም ይሰጣል።

ለበለጠ መረጃ የተፋጠነ እና የበለፀገ ትምህርት ክፍልን በስልክ ቁጥር 240-740-3110 ያነጋግሩ ወይም ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/።

## ማግኔት እና ኮንሰርሺያ ፕሮግራሞች

### ማግኔት ፕሮግራሞች

ሰብአዊ/ሂውማኒቲስ ኮሙኒኬሽን ፕሮግራም በዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ Jr እና በኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይሰጣል። ይህ ብዙ ፈርጅ ያለው የሰብአዊ/ሂውማኒቲስ ትምህርት ፕሮግራም በፅሁፍ፣ የሚዲያ ፕሮዳክሽን እና የአለም ጥናቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤እንዲሁም የተማሪዎችን የአካዳሚክ ምርምር ውጤታማ ለማድረግ ቋንቋ እና ሚዲያን በብቃት የመጠቀም ችሎታን በማዳበር ላይ ያተኩራል።

ሂሳብ/ሳይንስ/ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በሮቤርቶ ክሌመንት እና ታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ይሰጣል። ይህ ፕሮግራም ተማሪዎች ስለ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ኮምፒውተር ሳይንስ ፅንሰ-ሀሳቦች በተቀናጀ መልኩ እና በተፋጠነ ሁኔታ ግንዛቤያቸውን እንዲያዳብሩ ትምህርት ይሰጣል።

ወደ እነዚህ የሶስት አመት ፈርጀ ብዙ ፕሮግራሞች መግባት የሚቻለው በማዕከላዊ ደረጃ በሚከናወን የግምገማ ሂደት ነው። የፕሮግራም መረጃ እና የመግቢያ ሂደትን በተመለከተ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/middle/።

### የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ክንሰርቲየም

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ክንሰርቲየም (MSMC) ሶስት ትምህርት ቤቶችን ያቀፈ ነው፦ የአርጊል ማግኔት ትምህርት ቤት ዲጂታል ዲዛይን እና ልማት፤A. ማሪዮ ሎኢደርማን ማግኔት የፈጠራ እና ስነ ጥበባት ስራ፣ እና ፓርክላንድ ማግኔት ት/ቤት ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ለሁሉም ተማሪዎች የፈጠራን ግኝት የሚያበረታታ እና ጠንካራ የአካዳሚክ ስርአተ ትምህርት ይሰጣል፣ እንዲሁም ተማሪዎች በማግኔት ትምህርት ላይ ያተኮሩ ልዩ ኮርሶችን ለመውሰድ እድል አላቸው። MSMC ትምህርት ቤቶች በሙሉ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ፤ተፈታታኝና ጠንካራ ማግኔት ሞዴል ትምህርት ለማስተማር የተመሰረቱ ናቸው።

አርጋይል፤ፓርክላንድ እና ሎኢደርማን ክልል ውስጥ የሚኖሩ የ 5ኛ ክፍል ተማሪዎች ኮንሰርቲየም ማግኔት መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንዱን መምረጥ አለባቸው። በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሚገኙ 5ኛ ክፍል ተማሪዎች (እና 6ኛ ክፍል ተማሪዎች) ከእነዚህ ሶስት ትምህርት ቤቶች በአንዱ ለመማር በምርጫ ሂደት ማመልከት ይችላሉ። ይበልጥ ለማወቅ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/schools/msmagnet/.

## የተፋጠነ እና የበለጸጉ ኮርሶች

ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሂሳብ እና በማህበራዊ ጥናት ዘርፍ የተፋጠነ እና የበለፀጉ ትምህርቶችን ይሰጣሉ። እነዚህ ኮርሶች የተነደፉት ከአካዳሚክ እኩዮቻቸው ጋር ወደ ዳበረና የተፋጠነ ትምህርት ፅንሰ-ሀሳብ ጠልቀው በመግባት ለመማር ዝግጁ መሆናቸውን ለሚያሳዩ ተማሪዎች ነው።

## የተራዘሙ የትምህርት እድሎች

### የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተራዘሙ የትምህርት ጊዜያት እና የተራዘመ-ዓመት የሚሰጡ ፕሮግራሞች

የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት አመቱ የተራዘሙ የትምህርት እድሎችን ይሰጣሉ። የተራዘመ የትምህርት ቀን (ከመደበኛ የትምህርት ሠአት በኋላ) ፕሮግራሞች የተማሪዎችን ልዩ ፍላጎት ለማሟላት የተነደፈ ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጣሉ። እነዚህ የንባብ፣ የሂሳብ እና የፅሁፍ ጣልቃገብነት ፕሮግራሞች ተማሪዎች በክፍል ደረጃ ወይም ከክፍል ደረጃ በላይ ያለውን ሥርዓተ ትምህርት በተሳካ ሁኔታ ችሎታቸውን ማሻሻል እንዲችሉ የተነደፉ ናቸው።

## ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፣ በትምህርት ቤቶች መካከል የሚደረጉ የስፖርት ውድድሮች/ኢንተር-ስኮላስቲክ ስፖርቶች እና የአካዳሚክ ብቁነት

ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከትምህርት በኋላ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን ያካሄዳሉ፣ እና ብዙዎቹ ከመደበኛው የትምህርት ሠዓት በኋላ በተለያየ እንቅስቃሴ ለሚቆዩ ተማሪዎች የአውቶቡስ አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። እንቅስቃሴዎቹ ክለቦችን እና/ ወይም በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄዱ ስፖርቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት ሌላ ከት/ቤት ሠአት በኋላ ከአትሌቲክስ ውጪ በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የብቃት መስፈርት የለም።

ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተማሪዎች በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄድ የስፖርት ፕሮግራም ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ተማሪ በኢንተር-ስኮላስቲክ የአትሌቲክስ ቡድኖች ውስጥ ለመሳተፍ ወቅታዊ የአካል ብቃት ምርመራ ማስረጃ በትምህርት ቤቱ ፋይል ላይ ሊኖረው/ሊኖራት ይገባል፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የአካዳሚክ የብቃት መስፈርት ማሟላት አለበ(ባ)ት። በፎል ወቅት የሚደረጉ የቡድን ስፖርቶች የወንዶች እና የሴቶች ልጆች ሶፍትቦል እና ኮአድ ክሮስ-ካንትሪ ናቸው። በዊንተር/በክረምት ወቅት የወንዶች እና የሴቶች የቅርጫት ኳስ፣ እና በስፕሪንግ ወቅት የወንዶች እና የሴቶች እግር ኳስ ይካሄዳል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በስፖርት ውድድር ወቅት እርስበርስ ይወዳደራሉ።

ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ/ኢንተርኮላስቲክ አትሌቲክስ የአካዳሚክ ብቁነት መረጃ ለማግኘት እባክዎን MCPS ደንብ IQD-RB ይመልከቱ፦ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ ለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአካዳሚክ ብቁነት፣ www.montgomeryschoolsmd.org/ departments/policy/pdf/ iqdrb.pdf.

## የጆርጅ ቢ. ቶማስ፣ ሲር. ትምህርት አካዳሚ "የቅዳሜ ትምህርት ቤት/Saturday School"

ስለ በጀት ጥገኝነት፦ ዘጠኝ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች በቅዳሜ ቀናት ጠዋት በጆርጅ ቢ. ቶማስ የትምህርት አካዳሚ (ቅዳሜ ትምህርት ቤት)/ (Saturday School) ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ማበልጸግ፣ ማስጠናት፣ እና ስለ ትምህርታቸው የማማከር አገልግሎት የመስጠት ፕሮግራሞችንያካሄዳሉ። የጆርጅ ቢ. ቶማስ ሲር. የትምህርት አካዳሚ የተመሠረተው 1986 ዓ.ም "Mu Nu Chapter of Omega Psi Phi Fraternity/ወንድማማቾች" አማካይነት ለጥቁር አሜሪካውያን ትምህርት የላቀ ውጤት ለማቀዳጀት በታለመ የቅዳሜ ትምህርት ቤት ተነሳሽነት ነው። የአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ምንም ይሁን ምን የቅዳሜ ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ክፍት ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቹ፦ ብሌር፣ ክላርክስበርግ፣ አንስታይን፣ ጌትስበርግ፣ ኖርዝዌስት፣ ፔይንት ብራንች፣ ሮክቪል፣ ስፕሪንግብሩክ፣ ዊተን፣ እና ቨርቹዋል አማራጮች ናቸው። ስለ ቅዳሜ ትምህርት ቤት የማስጠናት ፕሮግራም እና ስለ ጆርጅ ቢ ቶማስ ሲንየር የትምህርት አካዳሚ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የካባቢዎን ት/ቤት ይጎብኙ፥ ወይም ይህንን ድረገጽ ይመልከቱ፦ www.saturdayschool.org

## የተማሪዎች ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም

ሁሉም ልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ደህንነታቸውን የሚደግፍ ሠላማዊና የሚያበለጽግ የትምህርት ቤት አውድ እንዲኖራቸው ይገባል። ሁሉም ተማሪዎች የመማር እድላቸውን ለማስፋት እንዲችሉ እንደዚህ አይነት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ አካባቢዎችን ማመቻቸት ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። MCPS ሁሉም ተማሪዎች የሚከተሉትን ለማድረግ የሚያስችላቸው አስፈላጊ ክህሎቶች እንዲኖራቸው ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።

- የትምህርት ቤት እና የሰፊው ማህበረሰብ ጥሩ አባል እንዲሆኑ
- ስሜታቸውን መቆጣጠር እንዲችሉ
- አካዴሚያዊ እና ማህበራዊ ጥንካሬን እንዲገነቡ
- ለራሳቸው ወይም ለጓደኞቻቸው አስፈላጊ ድጋፍን መለየት እና ማድረግ/ ማግኘት እንዲችሉ
- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት እንዲችሉ
- አዎንታዊ ይዘት ያለው ውሳኔ ማድረግ እንዲችሉ

ትምህርት ቤቶች ከእድሜ ጋር የሚመጣጠኑ እና በተማሪው(ዋ) ሁኔታ የሚለያዩ ውጤታማ የመከላከል እና የቅድመ ጣልቃ-ገብ ፕሮግራሞችን አዘጋጅተው ተግባራዊ ያደርጋሉ። እያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ MCPS ደንቦች ጋር የተጣለጠ የአካባቢ ዲሲፕሊን ፖሊሲ አለው። ትምህርት ቤቶች የሥነምግባር ትምህርትን እንደ ማስተማሪያ ፕሮግራሙ አካል አዋህደው ያስተምራሉ። ለእያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ረዳት የደህንነት ጥበቃ ተመድቧል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለልጃቸው ደኅንነት የሚያሳስባቸውን ነገር ወዲያውኑ ለት/ቤት አስተዳደር እንዲያሳውቁ ይበረታታሉ። ስለ ተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም ተጨማሪ መገልገያዎች እና መረጃዎች በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፦ www.montgomeryschoolsmd.org/ departments/studentservices/wellbeing/index-new.aspx and www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/coa. pdf። እንዲሁም፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ወደ ሳይበር ሴፍቲ የስልክ ቁጥር 301-279-3669 መደወል ይችላሉ።



## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልዩ/ስፔሻል ፕሮግራሞች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ የማስተማሪያ ሞዴሎችን ይጠቀማሉ። የመለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ እንደመሆንህ(ሽ) መጠን፣ በአካዳሚክ ጥንካሬዎችህ(ሽ)፣ በአካዳሚክ ዝንባሌህ(ሽ) እና በፍላጎትህ(ሽ) ላይ በመመስረት ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ እንድትችል(ይ) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለአንተ(ቺ) ሊገኙ የሚችሉ ልዩ የፕሮግራም አማራጮችን ማወቅ አስፈላጊ ነው። በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ፣ የአካዳሚክ ብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ ኮርሶችን እየመረጡ መሆኑን ለማረጋገጥ እነዚህን ፕሮግራሞች በቅድሚያ መመርመር አስፈላጊ ነው። ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልዩ ፕሮግራሞች፣ ኢንተርናሽናል ባካሎሬት (IB) ፕሮግራሞችን፣ የሥራ ዝግጁነት ጥናት ፕሮግራሞችን ወይም ልዩ የሥራ ተለማማጅነትን ጨምሮ መረጃ ለማግኘት ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/ በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የከፍተኛ ትምህርት ምደባ (AP) ኮርሶች ምርጫ ይሰጣል፣ እንዲሁም የኮሌጅ ኮርሶችን ማግኘት ይችላሉ።

የአካባቢያቸው ትምህርት ቤቶች (ሆም ስኩል) ኖርዝኢስት ኮንሰርትየም (ብሌክ፣ ፔይንት ብራንች፣ ስፕሪንግብሩክ) ወይም ዳወንካውንቲ ኮንሰርቲየም (ብሌር፣ አንስታይን፣ ኬኔዲ፣ ኖርዝዉድ፣ ዊተን) አካል የሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ምርጫ ሂደት ውስጥ ይሳተፋሉ። ስለዚህ ሂደት የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ Consortia Choice እና የማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎቶችን በስልክ ቁጥር 240-740-7800 ይደውሉ ወይም ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice

## የሜሪላንድ ዲፕሎማ መስፈርቶች

የሜሪላንድ ስቴት አራት መስፈርቶችን በተሳካ ሁኔታ ለሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመራቂዎች በሙሉ አንድ ዲፕሎማ እንዲሰጣቸው ይፈቅዳል፡- ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት ማግኘት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ማከናወን፣ እና በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አጠቃላይ ግምገማ ፕሮግራም (MCAP) በመባል የሚታወቀውን ተቀባይነት ባለው ደረጃ የትምህርት ምዘናዎችን ማለፍ። ሁሉም የኮርስ መስፈርቶች በሠንጠረዡ በቀኝ በኩል ተገልፀዋል።

## የኮሌጅ እና የሥራ ዝግጁነት (CCR)

ሜሪላንድ ወደፊት አክት ብሉፕሪንት፣ House Bill 1372 (HB1372)፣ ፌብሩዋሪ 2021 የፀደቀ። የመጨረሻ ግቡ የሜሪላንድን የትምህርት ስርዓት በሚቀጥሉት አስር አመታት ውስጥ በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ወደሆነ አለምአቀፋዊ ሞዴል መሻገር ነው። ብሉፕሪንት ሁሉም የመለስተኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የግለሰብ የሙያ ትምህርት ማማከር አገልግሎቶችን እንዲያገኙ እና 10ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ CCR እንግሊዝኛ እና ሂሳብ ችሎታ የሚገመገሙበትን የስቴት መስፈርቶች ያካትታል። ምዘናው የተማሪ ድምር GPA እና አልጀብራ 1 በክፍል ደረጃ ወይም MCAP አልጄብራ 1 አካዳሚክ ልህቀት እና በሂሳብ ትምህርት ችሎታ ላይ ያተኩራል። በ10ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ በእንግሊዝኛ እና በሂሳብ CCR መስፈርት ያላሟሉ ተማሪዎች ድጋሚ መመዘኛ ለመውሰድ የመዘጋጀት ድጋፍ በሚያገኙበት መርኃግብር ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ምዘናው በስቴት የተወሰነ እና የጸደቀ ተመሳሳይ ወይም የተለያዩ ምዘናዎችን ሊያካትት ይችላል። የትምህርት ቤት ካውንስለሮች እና ሰራተኞች ለእያንዳንዱ ተማሪ የተሻለውን የድጋፍ አቅጣጫ ለመወሰን ከተማሪዎች ጋር በቅርበት ይሰራሉ። 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ኮርሶችን በሚከተሉት መንገዶች ማግኘት ይችላሉ። የላቀ ደረጃ ምደባ (ኤፒ)፣ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት (CTE) እና/ወይም ዓለም አቀፍ ባካሎሬት (IB)። በተጨማሪም፣ ለጸደቁ የኮሌጅ ኮርሶች የሞንትጎመሪ ኮሌጅ (MC) መስፈርቶችን የሚያሟሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የጣምራ ምዝገባ አማራጭ ይኖራቸዋል።

## የኮርስ ክሬዲቶች

ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመዝግበው መማር እና የሚከተሉትን የሚያካትቱ ቢያንስ 22 ክሬዲቶችን ማግኘት (MCPS በቅድሚያ የተፈቀደላቸው አማራጭ ያላቸው ካልሆነ) አለባቸው።

<table>
<tr><th colspan="3">የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመመረቂያ መስፈርቶች</th></tr>
<tr><td>እንግሊዘኛ</td><td colspan="2">4 ክሬዲቶች በስነፅሁፍ እና መረጃዊ ጽሑፍ የተደራጀ ትምህርት፣ ጽሕፈት፣ ንግግር እና ማዳመጥ፣ ቋንቋ እና ሊተርሲ፣ከእነዚህም ውስጥ 1 ክሬዲት MCA ለእንግሊዘኛ ከሚውለው ጋር መጣጣም አለበት።</td></tr>
<tr><td>ስነ ጥበብ</td><td colspan="2">1 ክሬዲት ዳንስ፣ የሚድያ አርት፣ ሙዚቃ፣ ቲያትር፣ ወይም ቪዡዋል አርት፣ ወይም እነዚህን በማጣመር።</td></tr>
<tr><td>የጤና ትምህርት</td><td colspan="2">1 ክሬዲት</td></tr>
<tr><td>ሂሳብ</td><td colspan="2">4 ክሬዲቶች ፤ በአልጄብራ ትምህርት 1 የሚያካትተው MCA ለአልጀብራ ከሚሰጠው ትምህርት ጋር መመጣጠን አለበት፣ ወይም 1 ወይም ከዚያ በላይ ክሬዲቶች በተከታታይ በሚወሰዱት የሂሳብ ትምህርት ኮርሶች አልጄብራ 1 እንደ ቅድመሁኔታ መሟላት አለበት፣ እና 1 ከጂኦሜትሪ ትምህርት ጋር የሚሠላ ነው። ተማሪዎች በሁ/ደ/ት/ቤት በየአመቱ የሂሳብ ኮርስ ለመውሰድ መመዝገብ አለባቸው። ይኼውም ተማሪዎች ለመመረቅ ከሚያስፈልጋቸው የሂሳብ ትምህርት ከአራት በላይ ክሬዲቶችን ሊያስገኙላቸው ይችላል።</td></tr>
<tr><td>የአካል ማጎልመሻ ትምህርት</td><td colspan="2">1 ክሬዲት፣ ኦነርስ የጤና ትምህርት A/B</td></tr>
<tr><td>ሳይንስ</td><td colspan="2">3 ክሬዲቶች ቀጣይ ደረጃውን የጠበቀ የሳይንስ ትምህርት (NGSS)፤ ከ MCA ሳይንስ ጋር የሚሳለጥ 1 ክሬዲት በስነ-ህይወት/ላይፍ ሳይንስ፣ 1 ክሬዲት በፊዚካል ሳይንስ፣ እና 1 ክሬዲት የምድር/የጠፈር ሳይንስ ወይም NGSS ኮርስ ከምድር/ከጠፈር ሳይንስ ይዘት ጋር የተዋሃደ።</td></tr>
<tr><td>ሶሻል ስተዲስ/ ማህበራዊ ጥናት</td><td colspan="2">3 ክሬዲቶች፤ 1 የ ዩ.ኤስ. ታሪክ ክሬዲት፤ 1 የዓለም ታሪክ ክሬዲት፣ እና 1 ብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና MCA ስነመንግስት ጋር የሚስተካከል 1 የአካባቢ መንግስት ክሬዲት።</td></tr>
<tr><td>የኮምፒውተር ሳይንስ፣ ኢንጅነሪንግ ወይም የቴክኖሎጅ ትምህርት (TE)</td><td colspan="2">1 ክሬዲት ለ..የተመደበTE። ይሄንን መስፈርት የሚያሟሉ ኮርሶች የሚገኙት በኮርስ መግለጫ መጽሔት ውስጥ ሲሆን የሚያካትተውም የኮምፒውተር እና የአልጎሪዝሚክ (algorithmic) ትምህርት ወይም ችግሮችን የመፍታት እና የሰው ልጅ እምቅ ችሎታዎች የእውቀት፣ የመገልገያ መሳሪያዎች፣ እና የክህሎት ትግበራን ነው።<br><br>POS ላይ በመመስረት በስቴት የጸደቀ የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራም (POS) እና ቢያንስ 0.5 ክሬዲት ለማግኘት የተመረጡ ኮርሶችን ማጠናቀቅ አለባቸው።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶች፡<br>ለመመረቂያ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ክሬዲቶችን ከሚከተሉት ሦስት አማራጮች በአንዱ ማሟላት ይቻላል</td><td>ምርጫ 1</td><td>ምርጫ 2</td></tr>
<tr><td>በተመሳሳይ የአለም ቋንቋ 2 ክሬዲቶች፣ ይኼውም የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ ሁለት ክሬዲት እና 2 ክሬዲት በተመረጡ ኮርሶች የሚገኙ ክሬዲቶችን ሊያካትት ይችላል።</td><td>በስቴት የፀደቀ የጥናት ፕሮግራም (POS) ማጠናቀቅ እና ቢያንስ 0.5 ክሬዲት ወይም ከዚያ በላይ POS ላይ የተመሠረተ ተመራጭ ኮርስ</td></tr>
<tr><td>የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)</td><td colspan="2">75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰአታት<br><br>ከ 6ኛ ክፍል በኋላ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለትምህርት የሚመዘገቡ ወይም እንደገና ተመልሰው ለሚገቡ ተማሪዎች SSL መስፈርቱ በተመጣጣኝ ይያዝላቸዋል።</td></tr>
<tr><td colspan="3">በየክፍል ደረጃ ወቅታዊ የመመረቂያ መስፈርት በዚህ በይነመረብ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/graduation-requirements.aspx.</td></tr>
</table>

*2021 የሜሪላንድ ደንብ ኮድ (COMAR) ላይ በተደረጉ ለውጦች ምክንያት ይህ ህትመት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ሊቀየር ይችላል።

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በችሎታ ላይ የተመሠረተ/Merit ሰርተፍኬት

ከሜሪላንድ የሁ/ደ/ት/ቤት ዲፕሎማ በተጨማሪ፣የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተማሪዎች MCPS የከፍተኛ ችሎታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ዲፕሎማ ሊሰጣቸው ይችላል፦

- የከፍተኛ ችሎታ ኮርሶች—ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድንጋጌ መሠረት የላቀ ችሎታ ሰርተፍኬት (CM) ኮርስ ቢያንስ 12 ክሬዲቶችን ማግኘት አለባቸው። CM ኮርሶች ለድምር GPA አስተዋጽኦ የሚኖራቸው ኮርሱ የላቀ ደረጃ (AL) ተብሎ ከታወቀ ብቻ ነው። የከፍተኛ ችሎታ ሰርተፍኬት የሚያስገኙ ኮርሶች በሙሉ ውጤታቸው በፊደል መመዝገብ አለበት።
- የሒሳብ መስፈርት—ተማሪዎች MCPS አልጀብራ 2 ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ እና/ወይም ክሬዲት ማግኘት አለባቸው።
- የአማካይ ድምር ውጤት—ተማሪዎች የክፍል ውጤት ድምር አማካይ ቢያንስ 3.0 ነጥብ ማግኘት አለባቸው።

## የሜሪላንድ የቋንቋ ችሎታና ብቃት ማረጋገጫ/ Maryland Seal of Biliteracy

በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዎች መሥራት የሚችሉ የሁለተኛ ደረጃ ተመራቂዎች በኮሌጅ፣ በሙያ እና በተለያዩ 21ኛው ክፍለ ዘመን ማህበረሰብ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ለመሳተፍ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ናቸው። የሜሪላንድ የቋንቋ ችሎታና ብቃት ማረጋገጫ/Maryland Seal of Biliteracy የተማሪው(ዋ)ን ከፍተኛ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ የብቃት ደረጃ እውቅና የሚሰጥ በሜሪላንድ ህግ የተፈቀደ የማረጋገጫ ዲፕሎማ ነው። የሜሪላንድ የቋንቋ ችሎታና ብቃት ማረጋገጫ/Maryland Seal of Biliteracy ለማግኘት፣ተማሪ የሚከተሉትን ማድረግ ይጠበቅበ(ባ)ታል።

- የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት እንግሊዝኛ ምዘና ማለፍ 10፣ እና
- ACTFL (የአሜሪካ የውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ካውንስል) የብቃት መመዘኛ መሠረት መመዘኛዎቹ የሚለኩት ከእንግሊዝኛ ውጪ በሌላ ቋንቋ በማዳመጥ፣ በመናገር፣ በማንበብ እና በመጻፍ በሚያሳዩት ከፍ ያለ የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ብቃትን ማሟላት ነው።

ስለ መመዘኛዎቹ የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይህን ድረ ገጽ ይመልከቱ፦ https://marylandpublicschools.org/about/Documents/DCAA/World-Languages/biliteracy/MSDEACTFLAlignedAssessments.pdf.



# እንግሊዘኛ

የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ መርሃ ግብር አላማ የተማሩ እና መግባባት የሚችሉ አስተዋይ ምሁራንን መፍጠር ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ እና በመረጃ የበለጸገ አለም ላይ ሲደራደሩ ተገቢ የሆነ የቋንቋ ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሻገሩ፣ የተለያዩ ስብስብ ፅሁፎችን መተንተን፣ ሙግትና ክርክሮችን ማዘጋጀት፣ ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን ማቀናጀት፣ የተለያዩ አመለካከቶችን መመርመር እና የራስን አስተሳሰብ በማንፀባረቅ ረገድ አዳዲስ አካዳሚያዊ ተግባሮች ያጋጥሟቸዋል። ተማሪዎች ስነ ጽሑፍን በማንበብ፣ መረጃዊ ጽሑፎችን በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በመናገር እና በማድመጥ የቋንቋ ችሎታዎችን እና ስልቶችን ለማዳበር ይሰራሉ።

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | SSL ሰአቶች |
|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | 6ኛ ክፍል | ENG 1009 | |
| | 6ኛ ክፍል ከፍተኛ/የላቀ እንግሊዝኛ | ENG 1010 | |
| 7ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል እንግሊዘኛ | ENG 1011 | 10 |
| | 7ኛ ክፍል ከፍተኛ/የላቀ እንግሊዝኛ | ENG 1012 | 10 |
| 8ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል እንግሊዘኛ | ENG 1013 | |
| | 8ኛ ክፍል ከፍተኛ/የላቀ እንግሊዝኛ | ENG 1014 | |

የኮርስ መግለጫዎችን ለማወቅ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx።

# ሊተርሲ

## ሊተርሲ እና የምንባብ ድጋፍ

**ሊተርሲ**

ሊተርሲ በሁሉም የትምህርት ዘርፎች በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በመናገር፣ በማድመጥ እና በመመልከት የትኩረት፣ የፈጠራ እና የማሰብ ችሎታን መገንባት ነው። ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በአካዳሚም ሆነ በወደፊት የሙያ ስራ ረገድ ለወቅታዊ የሥራ ግብረኃይል ፍላጎት ዝግጁ ለመሆን በየእለቱ በሊተርሲ ትግበራ መሣተፍ አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች ይህንን በተለያዩ መንገዶች መተግበር ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡- የተለያዩ ውስብስብ ፅሁፎችን በማንበብ እና በመወያየት፣ አስተሳሰባቸውን ለማጥራት ተገቢ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ እና ተጨባጭና ግልጽ ማስረጃዎችን እና ምክንያቶችን በመጠቀም ሙግት/ክርክሮችን እና ማብራሪያዎችን በመገንባት ሊለማመዱ ይችላሉ። ምንም እንኳን እንደነዚህ ያሉት ክህሎቶች እንደየትምህርቱ ይዘት የሚለያዩ ቢሆኑም፣ ተማሪዎች ትክክለኛ የትምህርት ይዘት-ተኮር ዘይቤ እነዚህን ለማዳበር ተከታታይ እድሎች ይኖራቸዋል።

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # |
|---|---|
| ዲጅታል ሊተርሲ 1 | ENG 1030 |
| ዲጅታል ሊተርሲ 2 | ENG 1031 |
| ዲጅታል ሊተርሲ 3 | ENG 1032 |
| MS አካደሚክ ሊተርሲ | ENG 1029 |

ስለ ኮርስ መግለጫዎች ለመመልከት ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx።

# ምንባብ

**የምንባብ ድጋፍ**

ሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ እንዲያነቡ ማድረግ ግባችን ነው። በትምህርት አመቱ፣ ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስለ እያንዳንዱ ተማሪ የንባብ ደረጃ እድገት መረጃ ለአስተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ለመስጠት የአካዳሚክ ምንባብ ግስጋሴ መለኪያ (MAP-R) ግምገማዎችን ያካሄዳሉ። MAP-R በመደበኛነት የሚከናወነው 6ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ነው። ምዘናው ተማሪዎች ከአንዱ የክፍል ደረጃ ወደሌላው ሲሻገሩ የሚጠቀሙባቸው የጋራ የመረጃ ነጥቦችን መስጠት እና ለተማሪዎች የትምህርት እና የፕሮግራም ውሳኔዎችን ለመደገፍ ይረዳል።

ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ተለይተው የታወቁ ተማሪዎች በምንባብ ትምህርት ብዙ አማራጮች ይኖራቸዋል። በምንባብ የድጋፍ መስጫ ክፍለጊዜ ልዩ የንባብ ፕሮግራሞች ይሰጣሉ። ተማሪዎች በተራዘመ የትምህርት ጊዜ ወይም የቅዳሜ ፕሮግራም የመመዝገብ እድል ሊኖራቸው ይችላል።

# እንግሊዘኛ ቋንቋ ማዳበር (ELD)

እንግሊዘኛ ቋንቋ የማዳበር (ELD) ፕሮግራም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ ከክፍል ደረጃ የትምህርት ይዘት ጋር የተሣለጠ ጥራት ያለው እንግሊዝኛ ቋንቋን የማበልፀግ ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ ኮርሶች ተማሪዎች የትምህርት ይዘት እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውን እና ሂደቶችን እንዲማሩ እና ቋንቋን በብቃት ለመተርጎም እና ትምህርታቸውን በሁሉም የትምህርት ዘርፎች እንዲገልጹ በመርዳት ላይ ያተኩራሉ።

እነዚህ ኮርሶች የተነደፉት የእንግሊዘኛ ቋንቋን ለማዳበር በማንበብ፣ በመጻፍ፣ በመናገር እና በማዳመጥ ችሎታዎች ላይ በማተኮር ነው። ELD ኮርሶች በሰፋት የማዳመጥ እና የንግግር ልምምድ፣ የመስማት እና የቃል ንግግር ችሎታን ማዳበር፣ እና የማንበብ እና የመፃፍ ችሎታን ማበልፀግ ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ ኮርሶች የእንግሊዝኛ ቋንቋን ሰዋሰዋዊ አወቃቀሮች ማብራሪያ ይሰጣሉ፣ ይህም ተማሪዎች ስለተለያዩ መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ዘርፎች የበለጠ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ELD ትምህርቶች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ልማዶችን እና ባሕሎችን ግንዛቤ ሊያካትቱ ይችላሉ። ሁሉም ELD ኮርሶች 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ከሚገኙ የክፍል ደረጃዎች እና ስርአተ ትምህርት ጋር የተሣለጡ ናቸው።

እያደገ የመጣው የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) የአካዳሚክ ቋንቋ የብቃት ደረጃቸውን በተገቢው መንገድ ለመቃኘት፣ በጋራ እና በተናጠል እየተማሩ፤እጥፍ የትምህርት ክፍለጊዜያት በመማር የእንግሊዝኛ ቋንቋን ማዳበር ይችላሉ። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃት (ELP) ደረጃ WIDA ACCESS ፈተና ላይ ELP ደረጃ 1.0-4.4 ጋር በቀጥታ የተያያዙ ናቸው።

EMLs በዋና የእንግሊዘኛ ትምህርት ላይ በጋራ በማስተማር፣ በሴሚናር ኮርስ፣ ወይም በጣምራ ELD/ELA ሠርተፊኬት ያለው/ያላት መምህር አማካይነት ድጋፍ ያገኛሉ። ዋና የእንግሊዝኛ ትምህርት የሚወስዱ ተማሪዎች EMLs የእንግሊዘኛ ቋንቋ ብቃታቸውን የበለጠ ለማሳደግ EML ፕሮግራም ውስጥ የሌሉ አቻዎቻቸው ጋር የመገናኘት እድል ይኖሯቸዋል። በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማበልጸግ ፕሮግራማቸው፣ EML ውስጥ የሌሉ እኩዮቻቸው ጋር በሁሉም ሌሎች ዋና የትምህርት ዘርፎች ይገናኛሉ።

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ | SSL ሰአቶች |
|---|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 6 ለጀማሪ የመድብለ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs I) | ESL 1014 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 6 EMLs II | ESL 1017 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 6 EMLs III | ESL 1020 | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |
| 7ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 7 EMLs I | ESL 1015 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 7 EMLs II | ESL 1018 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 7 EMLs III | ESL 1021 | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |
| 8ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 8 EMLs I | ESL 1016 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 8 EMLs II | ESL 1019 | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 8 EMLs III | ESL 1022 | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |

### ሌሎች አማራጮች የሚያካትቱት:-

| በሦስት ወር መርሃ ግብር ለት/ቤቶች የሚሰጡ ኮርሶች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ | SSL ሰአቶች |
| 6ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 6 እያደገ የመጣ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች (EMLs) I | ESL 1014T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 6 EMLs II | ESL 1017T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 6 EMLs III | ESL 1020T | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |
| 7ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 7 EMLs I | ESL 1015T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 7 EMLs II | ESL 1018T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 7 EMLs III | ESL 1016T | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |
| 8ኛ ክፍል | እንግሊዝኛ 8 EMLs I | ESL 1016T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 8 EMLs II | ESL 1019T | እጥፍ ክፍለጊዜ | 10 |
| | እንግሊዝኛ 8 EMLs III | ESL 1022T | አንድ ክፍለጊዜ | 10 |

ስለ ኮርስ መግለጫዎች ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx.

| ውስን እና የተቋረጠ መደበኛ ትምህርት (SLIFE) ያላቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ኮርሶች | | | |
|---|---|---|---|
| | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ |
| SLIFE Literacy/ ሊተርሲ | MS Developmental Reading SLIFE 1 | ESL1023 | አንድ ክፍለጊዜ (SLIFE Tier 1 Literacy Only/ ሊተርሲ ብቻ) |
| | MS የንባብ እድገት/ Developmental Reading SLIFE 2 | ESL1024 | አንድ ክፍለጊዜ (SLIFE Tier 2 Literacy Only) |
| SLIFE Math | የሂሳብ አተገባበር ትኩረት ደረጃ 1 Mathematical Application Concents Tier 1 | MAT1018 | አንድ ክፍለጊዜ (SLIFE Tier 1 Math Only) |
| | የሂሳብ አተገባበር ትኩረት ደረጃ 2 Mathematical Application Concents Tier 2 | MAT1014 | አንድ ክፍለጊዜ (SLIFE Tier 2 Math Only) |

# ሂሳብ


የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ አሥራሁለተኛ ክፍል (Pre-K-12) የሒሳብ ትምህርት መርሃ ግብር ግብ ሁሉም ተማሪዎች የሂሳብ ችሎታቸውን፣ የሒሳብ ጽንሰ-ሀሳብን እና የሒሳብ አሠራሮችን በትክክል በመረዳት የሂሳብ ትምህርት ብቃትን እንዲያዳብሩ ማስቻል ነው። የመጨረሻው ግብ ሁሉም ተማሪዎች በሂሳብ ስሌት የማሰብ እና የማስላትን ችሎታ መገንባት እና ፕሮብሌሞችን በትክክል ለመፍታት የሂሳብን ፅንሰሃሳብ መጠቀም ማስቻል ነው።

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ |
|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | 6ኛ ክፍል ሂሳብ | MAT1005 | |
| | ሂሳብ 6 ወይም የላቀ ሒሳብ 7+ ላይ የሚተገበር ምርመራ Applied Investigations into Mathematics 6 or Accelerated Mathematics 7+ | MAT1003 | |
| | የተፋጠነ/የላቀ የሂሳብ ትምህርት 6+ | MAT1015 | |
| 7ኛ ክፍል | 7ኛ ክፍል ሂሳብ | MAT1006 | |
| | የተፋጠነ የላቀ የሒሳብ ትምህርት 7+ | MAT1016 | |
| | አልጀብራ 1 | MAT2000 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| 8ኛ ክፍል | 8ኛ ክፍል ሂሳብ | MAT1007 | |
| | አልጀብራ 1 | MAT2000 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| | ኦነርስ ጂኦሜትሪ/Honors Geometry | MAT2004 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ቅድመ ሁኔታ አልጀብራ 1 A/B |

### ሌሎች አማራጮች የሚያካትቱት:-

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ |
|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | አልጀብራ 1 | MAT2000 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| | ሒሳብ 180 ኮርስ 1 | MAT1010 | የተመራጭ ኮርስ ክሬዲት |
| 7ኛ ክፍል | ኦነርስ ጂኦሜትሪ/ Honors Geometry | MAT2004 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ቅድመሁኔታ:- አልጀብራ 1 A/B |
| | ሒሳብ 180 ኮርስ 1 | MAT1010 | የተመራጭ ኮርስ ክሬዲት በተመሣሣይ የክፍል ደረጃ ሂሳብ መመዝገብ አለበት። |
| 8ኛ ክፍል | ኦነርስ አልጀብራ 2/ Honors Algebra 2 | MAT2012 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ቅድመ ሁኔታዎች:- አልጀብራ 1 A/B እና ኦነርስ ጂኦሜትሪ A/B |
| | ሒሳብ 180 ኮርስ 1 | MAT1010 | የተመረጠው ኮርስ ክሬዲት በተመሣሣይ የክፍል ደረጃ ሂሳብ መመዝገብ አለበት። |

ስለ ኮርስ መግለጫዎች ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx።



# ሳይንስ



የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሳይንስ መርሃ ግብር ተማሪዎችን በሳይንስና ምህንድስና ጽንሰ-ሀሳቦች እና ልምምዶች የሳይንስ ቀጣይ ትውልድ ደረጃን በማጣመር የሣይንስ ይዘትን እንዲመረምሩ ያደርጋል። በሳይንስ እና በተጨባጩ ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነት ለተማሪዎች ለማሳየት የተካተቱ ጽንሰ-ሀሳቦችን በማሣለጥ በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ሶስቱን የሳይንስ ዘርፎች (መሬት፣ ስነህይወት እና ፊዚካል ሳይንስ) ለመማር በሳይንስና ምህንድስና ተግባራዊ ተሞክሮዎች ላይ ይሳተፋሉ። ልዩ በሆነ ክስተት ላይ የተመሰረተ የምርምር ጥያቄዎች እና የላብራቶሪ ምርመራዎች የፕሮግራሙ ዋና አካል ናቸው። ተማሪዎች ትክክለኛ ፕሮብሌሞችን እንዲመረምሩ እና የሳይንስ ፅንሰ-ሀሳቦችን በማገናዘብ ፕሮብሌም መፍታት እና የኦንላይን ምርመራዎች ያለማቋረጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ። የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሳይንስ መርሃ ግብር በሜሪላንድ ስቴት ተቀባይነት ካለው የሳይንስ ቀጣዩ ትውልድ ደረጃ (NGSS) እና የኮመን ኮር የስቴት ደረጃ የጠበቀ ሂሳብ እና ELA የስቴት እና የአካባቢ ሊተርሲ መስፈርቶች ጋር የተሣለጠ ነው። በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅ የተለየ የማስተማር ስልት ሁሉም ተማሪዎች አዳጋች እና አሳታፊ የሳይንስ ትምህርት አቀራረብን እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል። በስፕሪንግ ወቅት 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሜሪላንድ የተቀናጀ 8ኛ ክፍል የሳይንስ ምዘና (MISA) ይወስዳሉ፤ ይህም ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የሶስቱንም ክፍል የሳይንስ ፅንሰ-ሀሳብ እና ችሎታን ይሸፍናል። በዚህ ድረገጽ ላይ የበለጠ መረጃ ይገኛል፡- www.marylandpublicschools.org/about/Pages/DAAIT/Assessment/MISA/index.aspx.

በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሳይንስ ትምህርት ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ ከሚችሉት በርካታ የማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ስለ ውስጥ አካል ለማጥናት መበለት ነው። ተማሪዎች/ወላጆች/አሳዳጊዎች በእነዚህ ትምህርቶች የውስጥ አካልን ለማጥናት ለመበለት ከካውንቲው አማራጮች ውስጥ አንዱን ሊጠይቁ ይችላሉ። ሌሎች አማራጮች ቪዲዮ፣ ሠንጠረዦች/ቻርቶች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ የመማሪያ መጽሀፍት መደራረብ፣ እና በኮምፒውተር ምስል እውነተኛ አስመስሎ ማቅረብ የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ ፕሮግራምን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschools.org/curriculum/science

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | SSL ሰአቶች |
|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | የምድር ሳይንስ ምርመራ/ጥናት | SCI1022 | 10 |
| 7ኛ ክፍል | የስነ ህይወት ሳይንስ ትምህርት ምርመራ/ጥናት | SCI1023 | |
| 8ኛ ክፍል | የፊዚካል ሳይንስ ጥናት/ምርመራ | SCI1025 | |

ሌሎች አማራጮች የሚያካትቱት፡-

## ታኮማ ፓርክ እና ሮቤርቶ ክሌሜንቴ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማግኔት ኮርሶች

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | SSL ሰአቶች |
|---|---|---|
| የማግኔት ሳይንስ 6 ምርመራ/ጥናት | SCI1008 | 10 |
| የማግኔት ሳይንስ 7 ምርመራ/ጥናት | SCI1009 | |
| የማግኔት ሳይንስ 8 ምርመራ/ጥናት | SCI1010 | |

## ፓርክላንድ ማግኔት ኮርሶች

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
|---|---|---|
| የፕላኔት ምድር ተልዕኮ/Mission Planet Earth | SCI1012 | |
| የበረራ መርሕ | SCI1013 | |
| የሥነ ፈለክ/አስትሮኖሚ ጥናት | SCI1014 | |
| ሰው አልባ የጠፈር ምርምር | SCI1015 | |
| የላቀ ሰብአዊ የጠፈር ምርምር | SCI1016 | |
| የፕላኔት ምድር የላቀ ተልዕኮ/Adv Mission Planet Earth | SCI1017 | |
| Adv Comparative Planetology & Orbital Mechanics | SCI1018 | |
| አስትሮኖሚ የጠፈር ምርምር | SCI1019 | |
| Comparative Planetology & Orbital Mechanics | SCI1020 | |
| ሰብአዊ የጠፈር ምርምር | SCI1021 | |
| የምድር ስርዓት እና ዘላቂነት<br><br>Earth Systems and Sustainability A/B | SCI2110 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ ክሬዲት |
| ኦነርስ ፊዚክስ A/B | SCI2006 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሳይንስ ክሬዲት |
| አስትሮኖሚ A/B | SCI2068 A/B | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመራጭ ኮርስ ክሬዲት |

የኮርስ መግለጫዎችን ለመመልከት ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx።



## የማህበረሰብ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ

MCPS ተማሪዎች በጠንካራ፣ ተደራሽ፣ ጠቃሚ፣ እና አካታች የማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ ጥያቄዎችን በተመለከተ -- በታሪክ የተገለሉ ድምጾችን በርካታ አመለካከቶች ጭምር - በጥልቀት የማሰብ፣ በትኩረት የማንበብ፣ በግልፅ የመግባባት እና ማህበረሰባቸውን፣ አገራቸውን እና አለምን በማሻሻል እርምጃ ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋል።

በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማህበራዊ ጥናት መርሃ ግብር/ሶሻል ስተዲስ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ፖለቲካ እና ባህል ዘርፎችን በማጥናት ስለ ዓለም እና ስለ ዩናይትድ ስቴትስ የታሪክ ዘመን ቅደም ተከተል እና ጭብጥ ግንዛቤን ያዳብራል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሥራ እና ንቁ የህብረተሰብ ተሳታፊ ለመሆን ለመዘጋጀት በሚከተሉት የሊተርሲ እና የዜግነት ተግባሮች ይሳተፋሉ፦

- በታሪክ ተገልለው የኖሩ ድምጾችን በርካታ አመለካከቶች የሚያሳዩ ዋና ዋና ምንጮችን ጭምር የርካታ ታሪካዊ ምንጮች ትንተና፣
- ፅንሰ-ሀሳቦችን እና በፊት ያገኙትን እውቀት ለአሁኑ የነባራዊ ዓለም ችግር መፍቻ አተገባበር፣ እና
- የተለያዩ ቅርጸቶችን በመጠቀም የማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ ጽንሰ-ሀሳቦችን እና ዕውቀትን ስለ መግባባት፣ መተንተን እና በሙግት አጻጻፍ ላይ አጽንዖት መስጠት።

8ኛ ክፍል፤ ተማሪዎች የ 8ኛ ክፍል ማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ የሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና በስፕሪንግ ወቅት ይወስዳሉ፣ ይህም ከ 6ኛ እስከ 8ኛ የሶስቱንም ክፍል ደረጃዎች የማህበራዊ ጥናት ጽንሰ-ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ያካትታል።

| የክፍል ደረጃ | ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | SSL ሰአቶች |
|---|---|---|---|
| 6ኛ ክፍል | ስለ ዓለም ጥናት ታሪካዊ የመመራመር ጥያቄዎች 6 | SOC 1001 | |
| | የአለምአቀፍ ሰብአዊነት ታሪካዊ ምርምር 6 | SOC 1009 | |
| 7ኛ ክፍል | ስለ ዓለም ጥናት ታሪካዊ የምርምር ጥያቄዎች 7 | SOC 1004 | |
| | የአለምአቀፍ ሰብአዊነት ታሪካዊ ምርምር 7 | SOC 1010 | |
| 8ኛ ክፍል | ስለ አሜሪካ ታሪክ ታሪካዊ የምርምር ጥያቄ/ምርመራ 8 | SOC 1021 | 10 |
| | ስለ አሜሪካ ጥናት ታሪካዊ የምርምር ጥያቄ/ምርመራ 8 | SOC 1020 | 10 |

ስለ ኮርስ መግለጫ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx.



## ከቤት ውጪ የሚከናወን ስለ አካባቢ/ኢንቫሮመንት ትምህርት

6ኛ ክፍል ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከቤት ውጪ የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራም፣ "ከቤት ውጭ የአካባቢ ትምህርት/Outdoor Ed" በመባል የሚታወቀው ፕሮግራም ለተማሪዎች ሶስት ቀን ከመኖሪያ ቤት ውጪ ልምድና እውቀት እንዲያገኙ፣ "እኛ ተግባራችን እና ምርጫዎቻችን በውሃ ተፋሰስ ደህንነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሳድራሉ?" በሚል ጥያቄ ላይ ያተኮረ ልምድ ይቀስማሉ። አግባብነት ያላቸውን፣ አሳታፊ እና ሁለገብ ትምህርቶችን በመጠቀም፣ ተማሪዎች የአካባቢን ስነ-ምህዳር እና በዚህ ረገድ ያላቸውን ሚና ይቃኛሉ። ተፈጥሯዊ ዓለም ከቤት ውጪ የሚሰጥ የአካባቢ ትምህርት/Outdoor Ed በክፍል ውስጥ እና በላቦራቶሪ የሚሰጥ ሲሆን የሊተርሲ እና የሒሳብ ትምህርት ተዋህደው የሚሰጡበት ዘርፍ ነው። ይህ ተጨባጭ ትርጉም ያለው የውሃ ተፋሰስ ትምህርታዊ ልምድ የሚከተሉትን ትምህርታዊ ይዘቶች ያካትታል፦

- ስለ አካባቢ ለመመራመር ሳይንሳዊ ሙከራዎች ተግባር ላይ የሚውሉበት እና MCPS 6ኛ ክፍል ሥርዓተ ትምህርት በነባራዊ ዓለም ተጨባጭ ትምህርት የሚማሩበት የመስክ ተሞክሮዎች ይኖሩታል። የአካባቢ ሳይንስ ትምህርቶች በአካባቢ የውኃ ተፋሰስ ላይ ያተኩራሉ፣የአካባቢ ጅረት/ምንጭ የውሃ ጥራት ትንተና፣ የሕዝብ እንቅስቃሴን ለማጥናት በምስል ተቀናጅቶ የቀረበ/ሲሙሌሽን መጠቀም፣ እና የሰው ልጅ በአካባቢ ላይ ያለውን ተፅእኖ መመርመርን ያካትታል።
- ጥያቄ ለመጠየቅ፣ ስለ ትብብር፣ ሂሳዊ አስተሳሰብን ማዳበር እና ችግርን ለመፍታት ስልቶችን ስለ መፍጠር የተዘጋጁ አሳታፊ ትምህርቶች ናቸው።
- ተማሪዎች ከእኩዮቻቸው እና ከመምህራኖቻቸው ጋር መልካም ግንኙነቶችን የመገንባት ክህሎቶችን እንዲማሩ እና እንዲለማመዱ አወንታዊ ግንኙነቶችን ለመገንባት የተዋቀሩ እና የዘፈቀደ እድሎችን ያገኛሉ። ከቤት ውጪ የአካባቢ ትምህርት የሚሰጥበት ፕሮግራም በሚጠናቀቅበት ጊዜ 90 በመቶ በላይ ተማሪዎች አዲስ ጓደኛ ማፍራት መቻላቸው ሪፖርት ተደርጓል።
- ተማሪዎች የሚያደርጉት ምርጫ አካባቢን እንዴት እንደሚጎዳ ሲመረምሩ እና ለማሻሻል የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የአካባቢውን ተፈጥሮ ከመንከባከብ አንጻር ንቁ ተንከባካቢዎች እንዲሆኑ ተነሳሽነት እና እድል ይሰጣቸዋል። በአካባቢ/ኢንቫይሮሜንት ትምህርት እና ተግባራት የተማሪዎች የአካባቢ አገልግሎት ትምህርት ልምድ ያጎለብታሉ፣ ይህም 6ኛ ክፍል የሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ዋነኛ አካል ነው።

ከቤት ውጭ በሚከናወን ትምህርት፣ ተማሪዎች ከሶስቱ የትምህርት መስጫ ቦታዎች/ሳይቶች በአንዱ በዶርሚተሪ አይነት መኖሪያ ይቆያሉ፣ ማደሪያዎቻቸውን/ዶርሞችን ለመንከባከብ በትብብር ይሰራሉ፣ እና በምግብ ጊዜ እርስበርስ ተባብረው አገልግሎት ይሰጣሉ። ከእያንዳንዱ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ተማሪዎቻቸውን አጅበው ከቤት ውጪ የሚሰጥ የአካባቢ ትምህርት አስተባባሪዎች ጋር በመሆን ስለ አካባቢ በርካታ ትምህርት ያስተምራሉ። በትምህርት ቦርድ ድንጋጌ መሠረት ተማሪዎች ለፕሮግራሙ ለሚቆዩበት ቦታ ይከፈላል፣ የክፍያ አማራጮች እና ከክፍያ ነጻ የመሆን አማራጮች ይኖራሉ አሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲንየር ተማሪዎች ከቤት ውጪ ስለሚሰጥ የአካባቢ ትምህርት/Outdoor Ed ሲገልጹ፣ በ 12 ዓመት የትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት ካላቸው ሶስት በጣም ከሚታወሱ እና ከወደዷቸው የትምህርት ክንውኖች መካከል ይህንን በጣም የወደዱት ልዩ ልምድ አድርገው ይጠቅሳሉ።

## የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት

የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአካል ማጎልመሻ መርሃ ግብር በሶስት ዘርፎች ላይ ያተኩራል፣ ጤናን የሚያሻሽል የአካል ብቃት እና እንቅስቃሴ፣ የእንቅስቃሴ ችሎታ እና ጽንሰ-ሃሳቦች፣ እና የግል እና ማህበራዊ ሃላፊነት። እያንዳንዱ የትምህርት ይዘት ለታዳጊ ተማሪዎች በችሎታ ላይ የተመሰረተ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሪ ሃሳቦችን ይበልጥ ጥብቅ በሆነ ፕሮግራም ላይ እንዲተገበሩ ያስችለዋል። ተማሪዎች ከዓመቱ ውስጥ ሶስት ሩብ አመት ትምህርት ያገኛሉ። ትኩረቱ በትናንሽ (መደበኛ ያልሆነ ቁጥር) ጨዋታ እና ተግባራትን በተናጠል እንቅስቃሴ ማድረግ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ወደ ማሻሻል ይሸጋገራል። ተማሪዎች ግለሰባዊ የትኩረት ክህሎትን ከማሻሻል ባሻገር ከተናጠል ወደ ቡድን ውጤቶችን ለማሻሻል በሶስት አመታት ውስጥ ይሸጋገራሉ። ሁሉም ጨዋታዎች እና እንቅስቃሴዎች ስለ ግላዊ ብቃት እና በግለሰብ እና በቡድን ተለዋዋጭ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያለውን ወሳኝ አስተሳሰብ በማዳበር የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎት እና ችግሮችን የመፍታት ስልቶችን ያጎለብታሉ። Be Well 365 ጋር የሚዛመደው የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ከጤና ጋር የተገናኙ የዕድሜ ልክ አወንታዊ አመለካከቶችን እና ራስ መቻልን እና ራስን መቆጣጠር የሚያበረታቱ ባህሪያት ላይ አፅንዖት ይሰጣል።

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # |
|---|---|
| PE 6ኛ ክፍል | HPE1003 |
| PE 7ኛ ክፍል | HPE1004 |
| PE 8ኛ ክፍል | HPE1005 |

ስለ ኮርሱ መግለጫ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx.

## የጤና ትምህርት

አጠቃላይ የጤና ትምህርት ራስን መቻል፣ እና ራስን መቆጣጠር የሚደግፉ ከጤንነት ጋር የተገናኙ አወንታዊ አመለካከቶችን እና ባህሪያትን ያበረታታል፣ እንዲሁም ስለ ጤንነት-ሊተርሲ ክህሎቶችን እና የዕድሜ ልክ ደህንነትን ያበረታታል። በፕሮግራሙ ውስጥ አጽንዖት የተሰጣቸው የጤና አጠባበቅ-ሊተርሲ ተፅእኖዎችን መተንተን፣ መረጃ ማግኘት፣ የእርስ በርስ ግንኙነት/መስተጋብር፣ ውሳኔ መስጠት፣ ግብ መተለም፣ ራስን መምራት እና ማቀንቀን የመሳሰሉትን ያካትታል።

የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ የጾታዊ ግንኙነት ክፍል/ዩኒት ከእድሜ ጋር የሚጣለጥ ትምህርት "መፈቃቀድ/ስምምነት" ትርጉም እና የግል ገመና ገደብ የማክበር ስርዓት ትምህርቱ በሚሰጥበት በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ውስጥ ይካተታል። የጤና አጠባበቅ ትምህርት ከጤንነት ጋር የሚገናኙ የእድሜ ልክ አወንታዊ አመለካከቶችን እና ባህሪያትን በማጎልባረቅ ለሁሉም ተማሪዎች ራስን መቻል እና ራስን የመቆጣጠር ልምድ "Be Well 365" ጋር ያጣልጣል።

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # |
|---|---|
| 6ኛ ክፍል የጤና ትምህርት | HPE1000 |
| 7ኛ ክፍል የጤና ትምህርት | HPE1001 |
| 8ኛ ክፍል የጤና ትምህርት | HPE1002 |

ስለ ኮርሱ መግለጫ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx.

## የዓለም ቋንቋዎች

የአለም ቋንቋዎች መርሃ ግብር አላማ፡ ተማሪዎችን ከእንግሊዘኛ ቋንቋ በተጨማሪ በሌሎች ቋንቋዎች እና ባህሎች ብቁ የመግባባት ችሎታ እንዲኖራቸው ማዘጋጀት ነው። ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ የመግባባት ችሎታን ማዳበር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው 21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም አቀፋዊ ማህበረሰብ ውስጥ ለመሥራት እና ለስኬት ቁልፍ መንገድ ነው። ተማሪዎች በአለም ቋንቋዎች ብቃታቸውን እና የሌሎችን ባህሎች መሰረታዊ እሴቶች እና እምነቶች ሲረዱ፣ ትርጉም ያለው ግንኙነት ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑትን ክህሎቶች ያዳብራሉ። የአለም ቋንቋዎች ኮርሶች በቅደም ተከተል መወሰድ አለባቸው።

ተማሪዎች በመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ በተቻለ ፍጥነት የአለም ቋንቋዎችን ትምህርት እንዲከታተሉ ይበረታታሉ። በየትምህርት ቤቱ የትምህርት አቅርቦቱ ይለያያል። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች ናቸው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች በመሆናቸው እባክዎ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲት ስለሚያስገኙ ኮርሶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ገጽ 5 ይመልከቱ። የኮርሱ ቁጥሮች በቋንቋ- እና በክፍል ደረጃ- ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ከ 1A በስተቀር የሁሉም ኮርሶች ቅድመ ሁኔታ የቀደመውን ኮርስ በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ ወይም የአካባቢ ት/ቤት ምደባ ፈተና ማለፍ ነው።

### ደረጃ 1A/1B

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

ተማሪዎች ከዕለት ተዕለት ተሞክሮ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በቃል እና በፅሁፍ በተገቢ ሁኔታ ባህልን በሚያከብር ተስማሚ መንገድ መግባባትን መማር ይጀምራሉ። ሲያዳምጡ እና ሲያነቡ መሰረታዊ መረጃዎችን ይተረጉማሉ። የቃላት እና መሰረታዊ ሰዋሰዋዊ አወቃቀሮችን የሚማሩት በእነዚህ የተለመዱ ርዕሶች አውድ ውስጥ ነው። በኮርሱ ውስጥ ስለ ባሕል ተካቷል።

ማሳሰቢያ:- ደረጃ 1A እና 1B በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ ሙሉ አመት ኮርስ ይሰጣል። እንደዚያ ሲሆን፣ ተማሪዎች አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለማግኘት 1A እና 1B የሙሉ አመት ኮርስ ማለፍ አለባቸው።

### ደረጃ 2A/2B

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

ተማሪዎች ከእለት ተእለት ኑሮ ጋር በተያያዙ ርዕስ ጉዳዮች ላይ በቃልም ሆነ በፅሁፍ ተስማሚ በሆነ ባህላዊ መንገድ የመግባቢያ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። ሲያዳምጡ እና ሲያነቡ መረጃዎችን ይተረጉማሉ። የቃላት እና ሰዋሰዋዊ አወቃቀሮች የሚማሩት በእነዚህ ርዕሶች አውድ ውስጥ ነው። ስለ ባሕል በኮርሱ ውስጥ ተካቷል።

### ደረጃ 3A/B

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

ተማሪዎች የተለያዩ የተለመዱ ርእሶችን በቃል እና በፅሁፍ ተስማሚ በሆነ ባህላዊ መንገድ የመግባቢያ ችሎታቸውን ማዳበር ይቀጥላሉ። ሲያዳምጡ እና ሲያነቡ ዝርዝር መረጃዎችን ይተረጉማሉ። የቃላት ዝርዝር እና ይበልጥ የተወሳሰቡ ሰዋሰዋዊ አወቃቀሮችን የሚማሩት በእነዚህ ርዕሶች አውድ ውስጥ ነው። በኮርሱ ውስጥ ስለ ባህል ተካቷል።

| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | NOTES |
|---|---|---|
| ስፓንሽኛ ሊተርሲ 1 A/B | WLG2150 | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| ስፓንሽኛ ለስፓንሽ ተናጋሪዎች 1 A/B | WLG2141 | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| ስፓንሽኛ ለስፓንሽ ተናጋሪዎች 1 A/B | WLG2142 | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |

ስፓንሽኛ ለስፓኒሽ ተናጋሪዎች 1 A/B እና ስፓንሽኛ ለስፓንሽ ተናጋሪዎች 2 A/B በተወሰኑ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይሰጣሉ። ስፓንሽኛ ለስፓኒሽ ተናጋሪዎች ኮርሶች የሚሰጡት የመጀመሪያ ቋንቋቸው ለሆነ ወይም

በቤታቸው የሚነገረው ቋንቋ ስፓንሽኛ ለሆነ የተወሰነ ብቃት ላላቸው ተማሪዎች ቋንቋቸውን የሚያጎለብት ትምህርት ነው። እያንዳንዱ ኮርስ ታሪክን፣ ባህልን፣ ቋንቋን እና ከስፓንሽኛ ተናጋሪ ዓለም ጋር የተያያዙ ግንኙነቶችን ያጣምራል።

## የዓለም ቋንቋ ኢመርሽን

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢመርሽን ፕሮግራም ያጠናቀቁ ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤትም እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ። በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ያልተሳተፉ ተማሪዎች ቦታ ካለ ለኢመርሽን ፕሮግራም መፈተን ይችላሉ። የሚከተሉት መካከለኛ ትምህርት ቤቶች እነዚህን ኮርሶች ይሰጣሉ፡- ሲልቨር ስፕሪንግ ኢንተርናሽናል መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ስፓኒሽኛ/ፈረንሳይኛ)፣ ዌስትላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ስፓኒሽኛ)፣ ጌትስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ፈረንሳይኛ) እና ሁቨር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቻይንኛ)።

የኢመርሽን ቋንቋ ኮርሶች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የሚያስገኙ ኮርሶች ናቸው። በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሚወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ኮርሶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ገጽ 5 ይመልከቱ።

### ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የፈረንሳይኛ ቋንቋ ኢመርሽን
Grades 6–8 French Language Immersion
(WLG 2053 እስከ WLG 2055) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

የሁለት-ክፍለጊዜ የትምህርት መርሃ ግብር ተማሪዎች አንድ የቋንቋ ትምህርት እና አንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበራዊ ጥናት ትምህርት በፈረንሳይኛ ቋንቋ እያጠኑ የቋንቋ ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ።

### ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የስፓኒሽኛ ቋንቋ ኢመርሽን
Grade 6–8 Spanish Language Immersion
(WLG 2147 እስከ WLG 2149) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

ባለሁለት-ክፍለጊዜ የትምህርት መርሃ ግብር 6ኛ እና 7ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች አንድ የቋንቋ ትምህርት እና አንድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማህበራዊ ጥናት ትምህርትን በአንድ ክፍለጊዜ በስፓኒሽኛ እየተማሩ የቋንቋ ብቃት እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል። 8ኛ ክፍል ተማሪዎች አንድ የቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ይቀጥላሉ።

### 6ኛ ክፍል የቻይንኛ ቋንቋ ኢመርሽን
Grade 6 Chinese Language Immersion
(WLG 2034) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት

ይህ የአንድ-ክፍለጊዜ ኮርስ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኢመርሽን ፕሮግራም ያገኙትን የቋንቋ ችሎታ በመገንባት ይቀጥላሉ። ተማሪዎች 7ኛ ክፍል ወደ MCPS ቻይንኛ 2 ኮርስ ይሸጋገራሉ።



# ስነ ጥበብ/FINE ARTS

የስነ ጥበብ ትምህርት ለእያንዳንዱ ልጅ እድገት አስፈላጊ በመሆኑ ለተማሪዎች ጥሩ የተሟላ አለም አቀፍ ትምህርት በመስጠት ረገድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። ዳንስ፣ ሙዚቃ፣ ቲያትር እና ቪዥዋል አርት ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁነት ወሳኝ የሆኑትን አካዴሚያዊ ልህቀት፣ ችግር ፈቺነት፣ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ትምህርትን ያጎለብታሉ። የ 21ኛው ክፍለ ዘመን ተማሪ ፍላጎቶችን ለማሟላት የስነ ጥበብ ትምህርት ስነጥበባዊ ሊተርሲን በማሳደግ ረገድ (በፈጠራ፣ በመተወን/መድረክ ላይ በማቅረብ፣ ምላሽ በመስጠት እና የግንኙነት መረብ በመዘርጋት) ስነጥበባዊ እውቀትን በማዳበር ላይ ያተኩራል። ስነ ጥበብ ተማሪዎችን ከአዲሱ አለም እይታዎች እና ባህሎች ጋር ያስተዋውቃል፣ተማሪዎች የሌሎችን አመለካከት እንዲገነዘቡ እና የግል አመለካከትን በፈጠራ እንዲገልጹ ያስችላቸዋል። በሥነ ጥበብ ተሞክሮ፣ ተማሪዎች ራሳቸውን ችለው የተለያዩ እሳቢዎችን በራስ ተነሳሽነት የሚሰሩ ሰራተኞች እና ፈጣሪዎች ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስነጥበብ ፕሮግራሞችን ማግኘት ይችላሉ። ከ 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የስነጥበብ ይዘቶች ላይ ጥልቅ ጥናት/ስፔሻላይዝ ማድረግ ይችላሉ።

| ዳንስ | | |
|---|---|---|
| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ |
| MS ዳንስ/DANCE 1 | ART 1064 | የበፊት የዳንስ ልምድ አያስፈልግም። |
| MS ዳንስ/DANCE 2 | ART 1065 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS ዳንስ/Dance 1 ወይም ኦዲሽን/audition ማጠናቀቅ አለባቸው። |
| MS ዳንስ/DANCE 3 | ART 1066 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS ዳንስ/Dance 2 ወይም ኦዲሽን/audition ማጠናቀቅ አለባቸው። |

| ቪዥዋል አርት/VISUAL ART | | |
|---|---|---|
| ኮርስ | የኮርስ ኮድ # | ማሳሰቢያ |
| STUDIO ARTPATHWAY: ተማሪዎች የስነጥበብ ስራዎችን ለመስራት የተለያዩ ባህላዊ ARTmedia እና ቴክኒኮችን ይመረምራሉ፡ ሥዕል፣ ቅብ፣ ሕትመት፣ ቅርጻቅርጽ፣ ሴራሚክስ፣ እና ተግባራዊ ዕደ-ጥበብ። | | |
| MS የስቱዲዮ አርት/ STUDIO ART 1 | ART 1024 | የበፊት የአርት ልምድ አያስፈልግም። |
| MS የስቱዲዮ አርት/ STUDIO ART 2 | ART 1025 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS Studio ART1 ማጠናቀቅ ወይም ሠነድ/ፖርትፎሊዮ ማቅረብ አለባቸው። |
| MS የስቱዲዮ አርት/ STUDIO ART 3 | ART 1026 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS Studio ART2 ማጠናቀቅ ወይም ሠነድ/ፖርትፎሊዮ ማቅረብ አለባቸው። |
| MS ሥዕል መሣል/ DRAWING & 2D አርት/ART 3 | ART 1023 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS Studio ART2 ማጠናቀቅ ወይም ሠነድ/ፖርትፎሊዮ ማቅረብ አለባቸው። |
| MS ሴራሚክስ/ ቅርፅ የመስራት ጥበብ CERAMICS/ SCULPTURE 3 | ART 1039 | ተማሪዎች ለዚህ ደረጃ ብቁ ለመሆን MS Studio ART2ን ማጠናቀቅ ወይም ሠነድ/ፖርትፎሊዮ ማቅረብ አለባቸው። |

ስለ ኮርሱ መግለጫ ለማየት ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx።

| ዲጂታል አርት እና የፎቶግራፍ ፈለግ፦ ተማሪዎች የዘመኑን ተሞክሮዎች እና የኢንዱስትሪ ደረጃዎችን የሚያንፀባርቁ ዲጂታል ሃርድዌር እና የሶፍትዌር መድረኮችን በመጠቀም ዲጂታል አርት እና የፎቶግራፍ አሃሳስን ይመረምራሉ። | | |
|---|---|---|
| MS ዲጂታል አርት እና ፎቶግራፍ 1 | ART 1018 | ያለፈ የአርት ልምድ አያስፈልግም። |
| MS ዲጂታል አርት እና ፎቶግራፍ 2 | ART 1019 | ተማሪዎች MS ዲጅታል አርት/DIG ART እና የፎተግራፍ ጥበብ/PHOTO 1 ማጠናቀቅ አለባቸው። |
| MS ዲጂታል አርት 3 | ART 1022 | ተማሪዎች MS ዲጅታል አርት/DIG ART እና የፎተግራፍ ጥበብ/PHOTO 2 ማጠናቀቅ አለባቸው |
| MS የፎቶግራፍ ጥበብ 3 | ART 1020 | ተማሪዎች MS ዲጅታል አርት/DIG ART እና የፎተግራፍ ጥበብ/PHOTO 2 ማጠናቀቅ አለባቸው |
| የፈጠራ አርት ጥበብ፦ እነዚህ የአንድ አመት ኮርሶች ቪዥዋል አርት እና ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት አስተሳሰብን ያዋህዳሉ። በኮርሱ ማብቂያ ላይ፣ ተማሪዎች የሜሪላንድ ቴክኖሎጂ ትምህርት ደረጃ እና የብሔራዊ ቪዥዋል ደረጃዎችን ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ተማሪዎች የገሃዱን ዓለም ችግሮችን ይመረምራሉ፣ ከዚያም በጥልቅ የመመራመር አስተሳሰብ እና በሥነ ጥበባዊ ሂደት ትርጉም ያላቸው መፍትሄዎችን ለመንደፍ እና ለመፍጠር ይተጋሉ። ይህ ኮርስ የሮቴሽን አካል ሊሆን አይችልም። | | |
| MS የፈጠራ አርት እና ዲዛይን 1 | ART 1008 | ያለፈ የአርት ልምድ አያስፈልግም። |
| MS የፈጠራ አርት እና ዲዛይን 2 | ART 1007 | ተማሪዎች ደረጃ 1 የአርት መንገድ ኮርስ ማጠናቀቅ አለባቸው። |
| MS የፈጠራ አርት እና ዲዛይን 3 | ART 1016 | ተማሪዎች LEVEL 2 ART pathway ኮርስ ማጠናቀቅ አለባቸው። |

| አጠቃላይ ሙዚቃ | | |
|---|---|---|
| **ኮርስ** | **የኮርስ ኮድ #** | **ማሳሰቢያ** |
| ፒያኖ/PIANO, MS 1 | ART 1048 | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች ይሰጣል። |
| ፒያኖ/PIANO, MS 2 | ART 1049 | ተማሪዎች ፒያኖ/Piano, MS 1 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| ጊታር/GUITAR, MS 1 | ART 1043 | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ይሰጣል። |
| ጊታር/GUITAR, MS 2 | ART 1044 | ተማሪዎች ጊታር/Guitar, MS 1 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| አጠቃላይ ሙዚቃ/GENERAL MUSIC, MS 1 | ART 1030 | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይሰጣል። |
| አጠቃላይ ሙዚቃ/GENERAL MUSIC, MS 2 | ART 1031 | ተማሪዎች አጠቃላይ ሙዚቃ/General Music 1 ማጠናቀቅ አለባቸው |
| አጠቃላይ ሙዚቃ/GENERAL MUSIC, MS 3 | ART 1032 | ተማሪዎች አጠቃላይ ሙዚቃ/General Music 2 ማጠናቀቅ አለባቸው |

| የህብረት ሙዚቃ | | |
|---|---|---|
| **ኮርስ** | **የኮርስ ኮድ #** | **ማሳሰቢያ** |
| የቡድን ዝማሬ/የመዘሙር ጓድ፣ MS 1 የፈጠራ እሳቤ እና መዘመር | ART1040 A/B | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ይሰጣል። ይህ ኮርስ ተማሪዎች በስነ ጥበብ እና ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት አስተሳሰብን በማዳበር በሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች የሪፖርት ካርድ ላይ ክሬዲት ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች ዓመቱን ሙሉ መማር አለባቸው። |
| የቡድን ዝማሬ/የመዝሙር ጓድ/CHORUS, MS 2 | ART 1041 | ተማሪዎች የቡድን ዝማሬ/የመዝሙር ጓድ/Chorus, MS 1 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| የቡድን ዝማሬ/የመዝሙር ጓድ/CHORUS, MS 3 | ART 1042 | ተማሪዎች የቡድን ዝማሬ/የመዝሙር ጓድ/Chorus, MS 2 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |

| የሙዚቃ መሣሪያ | | |
|---|---|---|
| **ኮርስ** | **የኮርስ ኮድ #** | **ማሳሰቢያ** |
| ጀማሪ ባንድ MS እና የፈጠራ አስተሳሰብ | ART1037 A/B | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይሰጣል። ይህ ኮርስ ተማሪዎች ስነ ጥበብ እና ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት አስተሳሰብ በሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች የሪፖርት ካርድ ላይ ክሬዲት ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች ዓመቱን ሙሉ መማር አለባቸው። |
| ባንድ 1 MS እና የፈጠራ አስተሳሰብ | ART1033 A/B | የጀማሪ ባንድ ወይም የአንደኛ ደረጃ የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት ትምህርት ማጠናቀቅ አለባቸው። ይህ ኮርስ ተማሪዎች በስነጥበብ እና ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት ሂደት በሜሪላንድ ትምህርት ቤቶች ሪፖርት ካርድ ላይ ክሬዲት ይሰጣቸዋል። ተማሪዎች ዓመቱን ሙሉ መማር አለባቸው። |
| ባንድ/Band 2 | ART 1034 | ተማሪዎች ባንድ 1 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| ባንድ/Band 3 | ART 1035 | ተማሪዎች Band 2 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| ጀማሪ ኦርኬስትራ MS እና የፈጠራ አስተሳሰብ | ART1038 A/B | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይሰጣል። |
| ኦርኬስትራ 1 MS እና የፈጠራ አስተሳሰብ | ART1045 A/B | ጀማሪ ኦርኬስትራ ወይም የአንደኛ ደረጃ የሙዚቃ መሣሪያ መጫወት ትምህርት ማጠናቀቅ አለባቸው። |
| ኦርኬስትራ 2 | ART 1046 | ተማሪዎች ኦርኬስትራ 1 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |
| ኦርኬስትራ 3 | ART 1047 | ተማሪዎች ኦርኬስትራ 2 ወይም ኦዲሽን ማጠናቀቅ አለባቸው |

| ቲያትር | | |
|---|---|---|
| **ኮርስ** | **የኮርስ ኮድ #** | **ማሳሰቢያ** |
| ቲያትር 1 | ART 1061 | 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይሰጣል። |
| ቲያትር 2 | ART 1062 | ተማሪዎች ቲያትር 1 ማጠናቀቅ አለባቸው |
| ቲያትር 3 | ART 1063 | ተማሪዎች ቲያትር 2 ማጠናቀቅ አለባቸው |

ስለ ኮርሱ መግለጫ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፦ https://www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/middleschool/index.aspx.



## ስለ ቤተሰብ እና ተጠቃሚዎች/CONSUMER ሳይንስ

ስለ ቤተሰብ እና ሸማች ተጠቃሚዎች ሳይንስ (FACS) ፕሮግራሞች የግለሰብን፣ የቤተሰብን እና የህብረተሰብን ደህንነት በሚያሳድጉ ሂደቶች እና ክህሎቶች ላይ ያተኩራሉ። ፕሮግራሞቹ FACS ትምህርት ብሔራዊ ደረጃን የሚያንፀባርቁ እና ሂሳብ፣ የሳይንስ፣ የእንግሊዘኛ፣ እና ማህበራዊ ጥናትን/ሶሻል ስተዲስ ያካትታሉ። በፕሮጀክት ሥራ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ተማሪዎች ትክክለኛ ችግሮችን እንዲመረምሩ እና እንዲፈቱ ያበረታታል። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለማድረግ ተማሪዎች ተግባቦትን እና ሂሳዊ አስተሳሰብን እንዲሁም ወቅታዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ይማራሉ።

EDU 1000: ፈጠራ/CREATIVE FACS

EDU 1002: FACS 7ኛ ክፍል

EDU 1003: FACS 8ኛ ክፍል

## የመገናኛ ብዙሃን ሊተርሲ

**መብራት፣ ካሜራ፣ ሊተርሲ! (LCL!)
(ENG 1024 እና ENG 1025)**

ይህ ኮርስ በስነፅሁፍ እና ቪዡዋል ፅሁፎች የሊተርሲ ችሎታን ያዳብራል፣ የትብብር ክህሎትን ያሻሽላል፣ በራስ መተማመንን እና ተነሳሽነትን ይገነባል፣ እና በልዩ ልዩ ስልቶች ከፍ ያለ የአስተሳሰብ እድሎችን ይፈጥራል። ተማሪዎች ፊልሞችን እየተመለከቱ በጽሑፍ ላይ ያዩትን ወደራሳቸው ክህሎት ይቀይራሉ፣ እንዲሁም ምስሎችን እንዴት ማንበብ እንደሚችሉ እና ውጤታማ ቪዡዋል ግንኙነቶችን መፍጠር እንደሚችሉ ይማራሉ።

ኮርሱ የሚያተኩረው በሦስቱም የ MCPS የተንቀሳቃሽ ምስል ትምህርት ዘርፎች ላይ ነው - የአርት ስራዎችን ማንበብ/መተርጎም፣ ምስል፣ ገፅታን መፍጠር እና ማንቀሳቀስ፣ ተማሪዎች የማንበብ ክህሎታቸውን ወደ ተግባር ያሸጋግራሉ።

**መብራቶች፣ ካሜራ፣ ፊልም ሊተርሲ! (LCFL!) (ENG 1023)**

ይህ ኮርስ ይበልጥ የላቀ የሊተርሲ ክህሎትን ለማስተማር ፊልም እና የፊልም ታሪክ ጥናትን እንደ ዋና የትምህርቱ አካል ይሰጣል። ተማሪዎች ስለ ምስሎች እንቅስቃሴ/motion pictures ፊዚክስ እና ታሪክን እንዲሁም የፊልም ስራ ቴክኒኮችን በራሳቸው የቪዡዋል መስተጋብር ወይም ኮሙኒኬሽን ጋር እንዴት እንደሚተገበሩ ይማራሉ።

ተማሪዎች አንድ ልብ ወለድ እና የተመረጡ አጠር ያሉ ጽሁፎችን እና የስክሪን ድራማዎችን ያነባሉ። ስምንቱ ክፍሎች የፊልሞች ሥራ እንዴት እንደተጀመረ፣ ድምፅ አልባ የትረካ ፊልሞች፣ በንግግር የሚደመጡ/Talkies፣ ቀለማት የሌሏቸው፣ የዘውግ ክላሲክስ፡ የመሳሰሉትን ያካትታሉ የሆሊዉድ ወርቃማ ዘመን፣ ባህላዊና ያልተብረዘ/ክላሲክ ውርሶች የሆሊዉድ ወርቃማ ዘመን እና ከዚያ ባሻገር፣ ዘጋቢ ፊልሞች፣ አኒሜሽን፣ እና የፊልም እና የፊልም ፌስቲቫሎች ቢዝነስ። (የካሜራ መብራት ምጥጥን ማጠናቀቅ ሊተርሲ! አያስፈልግም።)

**መብራቶች፣ ካሜራ፣ የሚዲያ ሊተርሲ! (LCML!) (ENG 1027)**

ይህ ኮርስ ስለ መገናኛ ብዙሃን፣ ስለ ታሪኩ መሰረታዊ ተዛማጅ የፊዚክስ ፅንሰ-ሀሳቦችን የበለጠ የላቀ የሊተርሲ ክህሎቶችን ለማስተማር እንደ ዋና የትምህርቱ አካል በማድረግ ኮርስ ይሰጣል። መብራቶች፣ ካሜራ፣ ሚዲያ ሊተርሲ! ከጥንት ጀምሮ በግንኙነት ታሪክ እና ፊዚክስ ላይ ያተኮረ የመገናኛ ብዙሃን የጊዜ አመጣጥን በተርባዶር እና በግሪቶች ተረክ እስከ ዛሬው የመገናኛ ብዙሃን ዓለም ያለውን ተያያዥ ትምህርት ይሰጣል። የትምህርት ክፍሎቹ/ዩኒትስ በቃል የሚነገሩ ታሪኮች፣ ማተሚያዎች፣ ጋዜጦች እና የህትመት ማስታወቂያዎች፣ ስለ ፎቶግራፍ እና ፊልም፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተሮች እና ኢንተርኔት፣ እንዲሁም ስለ ሚዲያ እና ስለ ዓለማችን የሚያካትቱ ናቸው። ተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዩኒት/ክፍል ውስጥ ተዛማጅ የብዝሃ ሚድያ/መልቲሚዲያ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃሉ። (የካሜራ ብርሃን ማመጣጠን፣ ሊተርሲ! ወይም መብራቶች፣ ካሜራ፣ ፊልም ሊተርሲ! ማጠናቀቅ አያስፈላጊ አይደለም)

ይህ LCL! ተከታታይ ኮርስ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው ሲሆን፣ ቀላል የተለያየ ግንዛቤን ለመፍጠር፣ ቪዡዋል/እይታ፣ የማድመጥ እና የአካል እንቅስቃሴ ተዛማጅነትን ትምህርት ያጠቃልላል። LCL! ስትራንድ ትኩረት በሁለቱም የፅሁፍ እና የእይታ ፅሁፎች ሊተርሲ ላይ ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀምን፣ የትብብር ክህሎቶችን ማዳበር፣ በራስ መተማመንን መገንባት እና ተነሳሽነትን የሚያሳድግ እና የላቀ ደረጃ አስተሳሰብ እድሎችን የሚፈጥር ነው።

## ሳይንስ፣ ቴክኖሎጅ፣ ምህንድስና/ ኢንጂነሪንግ እና ሂሳብ (STEM)

### የኮምፒውተር ሳይንስ ~ ምህንድስና/ኢንጂነሪንግ ~ የቴክኖሎጂ ትምህርት

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት STEM ተመራጭ ኮርሶች ለሁሉም ተማሪዎች የኮሌጅ፣ ለሙያዊ ስራ እና በፍጥነት እየተለዋወጠ ላለው 21ኛው ክፍለ ዘመን የሥራ ግብረ ሃይል ፍላጎትን ለማሟላት በሚደረግ ዝግጅት አስፈላጊ የግንባታ ጡብ/ማዕዘን ናቸው። STEM ኮርሶች ተማሪዎች ችግሮችን ለመቃኘት እና ለመፍታት የሂሳብ፣ የሳይንስ እና የቴክኒክ እውቀታቸውን በተግባር እንዲያውሉ የሙከራ ትምህርት ይሰጣል። MCPS ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሚገባ የተሟላ ትምህርት ለመስጠት ቁርጠኛ ሲሆን ይኼውም፦ አሳታፊ፣ በተግባር እየሠሩ የሚማሩት፣ እና በኮምፒውተር የሚታገዙ ትምህርቶች ናቸው። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት STEM ተመራጭ ኮርሶች ተማሪዎችን ኮዲንግ፣ የኮምፒውተር ሳይንስ፣ ምህንድስና፣ ሮቦቲክስ፣ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ እና የዲዛይን/የንድፍ ሥራ ሙያዎችን ያስተምራሉ። ይህ ፕሮግራም ችግሮችን የመፍታት ፈጠራን ማጎልበት እና STEM ጋር የተያያዙ በርካታ የጥናት እና የስራ መስኮችን ማሰስን ያበረታታል።

ለተማሪዎች በርካታ STEM የሙያ መስክ ልምዶችን ለማግኘት፣ ጠንካራ የኮምፒዩተር ሳይንስ እና የምህንድስና ኮርሶችን የመሳሰሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ክህሎት እና ዕውቀትን ለመገንባት፣ እና በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት የማግኘት እድልን ለመፍጠር፣በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲማሩ የሚመከሩ የኮርስ ዝርዝሮች የሚከተሉት ናቸው፦



| 6ኛ ክፍል MS ኮድዲንግ፣ ምህንድስና እና ሮቦቲክስ ዲዛይን የማርክ መስጫ ወቅት STEM ተመራጭ ኮርሶች* | |
|---|---|
| ኮድ መፍጠር እና በኮምፒውተር የሚደረጉ ጨዋታዎችን መፍጠርና ማጎልበት (ITC 2069)<br>ተማሪዎች የጥሩ ጨዋታ ዲዛይን እና የተለያዩ የጨዋታ ዘውጎችን እንዲሁም መሰረታዊ የቪዲዮ ጨዋታዎችን ኮድ የመፍጠር ፅንሰ-ሀሳቦችን በኮምፒውተር ማሰስ፣ መጫወቻ መድረክ መፍጠር፣ ማስጀመር እና ሌሎችንም ይማራሉ። ተማሪዎች በኮምፒውተር የመጫወቻ ዲዛይኖችን ሲሰሩ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን የመለየት አስተሳሰብን ይተገብራሉ። ተማሪዎች ከተለያዩ የፕሮግራሚንግ ቋንቋዎች ጋር ይተዋወቃሉ። | ቴክኖሎጂ እና ምህንድስና መግቢያ (ENR 1022)<br>ተማሪዎች ከቴክኖሎጂ ሲስተሞች ጋር ይተዋወቃሉ፣ አዳጋችና ውስብስብ ሁኔታዎች ላይ የምህንድስና ዲዛይን አሠራርን ይማራሉ እና ይተገበራሉ። ተማሪዎች TinkerCAD በመጠቀም በኮምፒዩተር የታገዘ የዲዛይን አሠራር ጋር ይተዋወቃሉ። |
| የምህንድስና ዲዛይን እና ሞዴሊንግ (ENR 1023)<br>ተማሪዎች ውስብስብ የምህንድስና አሠራር ተግዳሮቶችን ለመፍታት TinkerCAD በመጠቀም የአይሶሜትሪክ ንድፍ፣ በብዙ ጎን/ማእዘን የሚታይ ምስል፣ እና በኮምፒዩተር የታገዘ የዲዛይን ሥራ ቴክኒክ ይጠቀማሉ። | ሮቦቲክ ዲዛይን 6 (ITC 2068)<br>ተማሪዎች ለኮምፒውተር ትእዛዝ ምላሽ የሚሰጡ ናሙናዎችን/ሞዴሎችን በአካላል ለመሥራት ኮድ እና የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ ክህሎቶችን እና ችግር የመፍታት ስልቶችን ተግባራዊ ያደርጋሉ። ተማሪዎች ተጨባጭ የሆኑ የህይወት ተሞክሮዎችን አዳጋች ሁኔታዎች ስለመፍታት በሚማሩበት ጊዜ በትብብር ይሠራሉ፣ ይወያዩባቸዋል፣ ለአንድ ውስብስብ ችግር ደረጃ-በ- ደረጃ ግልጽ የሆነ መፍትሄን በመለየት ሂደት በመታገዝ ይሠራሉ፣ ፕሮግራም፣ የኮምፒውተር ፕሮግራም ኮድ በመጠቀም ስህተቶችን ያርማሉ/ያስተካክላሉ፣ እና ናሙናዎችን/ሞዴሎችን ይፈጥራሉ። |

*ትምህርት ቤቶች ከእነዚህ ሩብ-አመት ከሚወሰዱ ኮርሶች ከ1 እስከ 4 ያህሉን ሊሰጡ ይችላሉ።

| የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 7ኛ ክፍል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መርሆዎች፣ ሳይበር ሴኩሪቲ፣ እና የምህንድስና/የኢንጂነሪንግ ኮርሶች የማጠናቀቂያ "STEM ELECTIVES" ተመራጮች* | |
|---|---|
| IT መርኖች፡- ዲጂታል ሲስተምስ 7 (ITC 2070)<br>ተማሪዎች ቁልፍ የሆኑ የኮርስ ይዘቶችን/ክፍሎችን በመመርመር ዲጂታል ሲስተሞችን እና መሳሪያዎችን ይቃኛሉ። ሃርድዌር እና ሶፍትዌሮችን በታትነው በመለያየትና በመገጣጠም ይጀምራሉ፣ ከዚያም ግብአት እና ምርት/ውጤት መሳሪያዎችን/devices፣ ማከማቻ እና የማቀነባበሪያ ክፍሎችን ይመረምራሉ። ተማሪዎች ችግሮችን ለመፍታት ዲጂታል ሲስተሞችን በመጠቀም የተለያዩ ችግር ፈቺ ተግባራዊ ስልቶችን ይማራሉ። ተማሪዎች ስለ ሶፍትዌር አፕሊኬሽኖች፣ ቅጥያዎች እና ክላውድ-ተኮር ፕሮግራሞች ግንዛቤያቸውን የበለጠ ያዳብራሉ። | IT መርኖች፡- የሳይበር ደህንነት/Cybersecurity (ITC 2071)<br>ተማሪዎች መረጃ በበይነ መረብ እና በመገናኛ መረቦች እንዴት እንደሚጓዙ እና የኤሌክትሮኒክስ መረጃን ደህንነት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ይማራሉ። የገሃዱ ዓለም የሳይበር ደህንነት ችግሮች ተጠቃሚዎችን፣ የበይነመረብ ስርዓቶችን/ሲስተሞችን እና የአውታረ መረብ ደህንነትን ለመጠበቅ ከአሁናዊ ምርጥ ተሞክሮዎች ጋር በመቃኘት ይዳሰሳሉ። ተማሪዎች የተለያዩ የሳይበር ደህንነት ሙያዎችን ይማራሉ። የኮርሱ ይዘት ከኮምፒዩተር ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የህግ እና የስነምግባር ጉዳዮችን ያካትታል። |
| ፈጠራ እና ምህንድስና ዲዛይን 7 (ENR 1025)<br>ተማሪዎች በቴክኖሎጂ እድገት ውስጥ የፈጠራን አስፈላጊነት እና ፈጠራ በቴክኖሎጂ እድገት ውስጥ ያለውን ሚና ይማራሉ፤ እንዲሁም የምህንድስና-አስተሳሰብ ክህሎቶችን እና የቴክኒክ ክህሎቶችን እያንዳንዱን የምህንድስና ዲዛይን ሂደትን በማጠናቀቅ ይተግብራሉ፣ ለነባራዊው ዓለም ተግዳሮቶች በፈጠራ ክህሎታቸው መፍትሔ ይፈጥራሉ። ተማሪዎች ቴክኒካዊ ምስሎችን እና በኮምፒውተር የተደገፈ የንድፍ ሥራዎችን ይማራሉ ወይም ያዳብራሉ። | ተግባራዊ የምህንድስና ንድፍ/ዲዛይን/MS Applied Engineering Design (ENR 1024)<br>ተማሪዎች ማህበረሰባዊ አመለካከቶችና እውነታዎች በቴክኖሎጂ እድገት ላይ እንዴት ትጽእኖ እንደሚያደርጉ ይማራሉ፤ እና የምህንድስና ዲዛይን ሂደትን፣ የምህንድስና-አስተሳሰብ ክህሎቶችን እና በኮምፒዩተር የታገዘ ዲዛይንን ጨምሮ ቴክኒካዊ ክህሎቶችን በመጠቀም ለገሃዱ አለም ተግዳሮቶች የምህንድስና መፍትሄዎችን ያጎለብታሉ። |

*ትምህርት ቤቶች ከእነዚህ ሩብ አመት-ከሚዘልቁ ኮርሶች ውስጥ ከ1 እስከ 4 ያህሉን ሊሰጡ ይችላሉ።

| ሌሎች 7ኛ ክፍል ተመራጭ ኮርሶች |
|---|
| የኮምፒውተር መተግበሪያዎች ከትንታኔ ጋር/Computer Applications with Analysis (ITC1002) |

## 8ኛ ክፍል STEM ተመራጭ ኮርሶች

8ኛ ክፍል ተማሪዎች ክሬዲት የሚያስገኝ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቴክኖሎጂ ትምህርት ኮርስ የመውሰድ እድል አላቸው። በእነዚህ ኮርሶች ላይ፣ MCPS ኮዲንግ፣ ሮቦቲክስ፣ እና የምህንድስና ዲዛይን አሠራሪችን ለማጥናት "Code.org እና Project Lead the Way" የመሣሰሉ የብሄራዊ ድርጅቶችን ስርዓተ ትምህርት/ካሪኩለም ከውጭ ተጠቅሟል።

| |
|---|
| መሠረታዊ የኮምፒውተር ሳይንስ/Foundations of Computer Science TE A/B (ITC2083)#<br>የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |
| የኢንጂነሪንግ ንድፍ/ዲዛይን ሥራ መግቢያ/Introduction to Engineering Design A/B (TEC 2017 A/B))#<br>የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዋና ዋና የክሬዲት ኮርሶች፡- አልጀብራ 1 ወይም ከዚያ በላይ |
| የግሎባል ቴክኖሎጂ ሲስተምስ/Global Technology Systems (ENR 1021) |
| ድረ ገጽ ማልማት/Website Development A/B (ITC 2025 A/B)*<br>የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት |

#ይህ ኮርስ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምረቃ አንድ የቴክኖሎጂ ትምህርትን ክሬዲት ያሟላል።
*አሁን ለሚያስተምሩት ትምህርት ቤቶች ብቻ የተገደበ



እባክዎ ስለ 2025-2026 የተመራጭ ኮርስ አማራጮችን በሚመለከት ከልጅዎ ትምህርት ቤት ያረጋግጡ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

<table>
<tr><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td><td>በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Improvement<br>Well-Being and Student Services<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-3109 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, ዐወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org



Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

አሳታሚ፡- Department of Materials Management for the Office of Curriculum and Instructional Programs
0436.25 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 12/24